# ዕዝራ

የዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት ግብና ዓላማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ይዘት ያላቸውን ቅዱሳንን የሚመግቡ ከአጫጭር መጣጥፎች እስከ ትልልቅ የማስተማሪያ መርጃዎች በማዘጋጀት ቤተ ክርስቲያንን መደገፍና በዚህም እግዚአብሔርን ማክበር ነው።

ቁጥር ፳፫ - ኅዳር ፪ሺህ ፮ ዓመተ ምሕረት NOVEMBER 2013 ezralit@gmail.com

## የመጋቢዎች አባዜ

## እስላም እና ክርስትና (ንጽጽራዊ አቀራረብ)

የመጽሐፍ ሒስና ግምገማ - ክፍል ሦስት

## ተመችቶኛል አልተመቸኝም

ሰላምና ጤና ይስጥልኝ፤

በዚህ ስርጭት ሁለት መጣጥፎችና አንድ ተጨማሪ አቅርቤአለሁ።

እስላምና ክርስትና (ንጽጽራዊ አቀራረብ) በዶ/ር ሙሓመድ ዓሊ ኣልኹሊ የተጻፈና ወደ አማርኛ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስን አጨማልቆ የሚያቀርብ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉን ለመገምገምና ምላሽ ለመስጠት እና መጽሐፉን ለማሔስ ብቻ ሳይሆን በትክክል ኢስላም እና ቁርኣን የሚያስተምረውን ምንነት ለመረዳትም እንዲሆን ከመጽሐፉ በመነሣት በተከታታይ እያቀረብኩት ነኝ። ባለፈው ክፍል ሁለትን ተመልክተን ነበር፤ ይህ ክፍል ሦስት ነው። ይቀጥላል።

የመጋቢዎች አባዜ ከልባቸው እየተጉ የጌታን ሕዝብ እያገለገሉ የሚገኙ የተመሰገኑ ብዙ መጋቢዎች አሉ። እንዲህ ያሉ መጋቢዎች ከኖሩን የተባረክን ነን፤ እግዚአብሔር ይመስገን። ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን በመጋቢዎች አገልግሎቶች ዙሪያ በጉልህ እየታዩ ያሉ የተቃወሱ አዝማሚያዎች አሉ። በመልካም አገልጋዮች የተባረክን ጌታን እያመሰገንን የምናዝንባቸው ያሉን ደግሞ እንጸልይ። ከጸሎት በኋላ ደግሞ እንጠይቅ። ስለተቃወሱ አንዳንድ አዝማሚያዎች ከበርካታ ጥቂቶቹንና በወጉ የታዘብኳቸውን በዚህ ትንሽ መጣጥፍ በአጫጭሩ ላነሣ እወዳለሁ።

የተመችቶኛልና አልተመቸኝም አንቀጾቼ ብሎ ሰሎሞን ጥላሁን ቅሬታውንና ደስታውን ከምኞቱ ጋር ለውሶ የጻፈውን አንቀጾች አስቀምጫለሁ። የሰሎሞንን አንድ ግጥምም ጨምሬአለሁ።

መልካም ንባብ።

ዘላለም መንግሥቱ / ዕዝራ ስነ ጽሑፍ፥

# የመጋቢዎች



# አባዜ

*ስለዚህ፥ እረኞች ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ . . .*

ሕዝ. 34፥7 እና 9

## ከስያሜው እንነሣ

በተለምዶ በእንግሊዝኛ ‘ፓስተር’ ለሚለው ቃል የምንጠቀመው ቃል መጋቢ የሚል ሲሆን መጋቢነትና እረኝነት የተለያዩ ቃላት ናቸው። ፓስተር ከሮማይስጥ (ላቲን) መሠረት የተገኘ ቃል ሆኖ በቀጥታም በምሳሌም እረኛ ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን መጋቢ የሚለው ቃል *οἰκονόμος* የሚል ነው። የቤት አስተናባሪ፥ አስተዳዳሪ፥ ሕግ አስጠባቂ፥ ኃላፊ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን የግምጃ ቤት ዋና ሰው፥ የንብረት ጠባቂና ኃላፊ እንደማለት ነው፤ ዘፍ. 15፥2። በአዲስ ኪዳን የንብረት አስተዳዳሪ ነው፤ ሉቃ. 16፥1-8፤ ገላ. 4፥2። በሮሜ 16፥26 ያለው ቃል ከከተማ ከንቲባ በታች ያለ የንብረት ሹም እንደማለት ነው። ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አንጻር ከተመለከትነው መጋቢ የሚለው ቃል በተለምዶ ፓስተር የሚባለውን ሰው ሳይሆን የንብረትና ገንዘብ ኃላፊ የሆነውን አደራ የተቀበለ ሰው የሚያመለክት ሹመት ነው። አንዳንድ መጋቢዎች ከገንዘብ ጋር ያለልክ የሚጣበቁት ምናልባት ለዚህ ሳይሆን ይቀራል?

እረኛ ወይም እረኞች በኤፌ. 4፥11 እንደተጻፈው ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጡ ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የተጻፈ ቃል ነው። ይህ ቃል *ποιμένας* በአዲስ ኪዳን ቋንቋ በሉቃ. 2፥8-18 ከተጻፉት እረኞች ጋር ቃሉ አንድ ነው። በ1ጴጥ. 5፥4 ጴጥሮስ የእረኞች አለቃ ብሎ ስለ ክርስቶስ ሲናገር ከስሩ ስላሉ እረኞች መናገሩ ነው። በዮሐ. 21፥15-17 ጌታ ስምዖን ጴጥሮስን ግልገሎቼን አሰማራ፥ ጠቦቶቼን ጠብቅ፥ በጎቼን አሰማራ ሲለው ይህን በበግ እረኛ ኃላፊነት የተመሰለውን አደራ መስጠቱ ነው። ጌታ እርሱ ራሱ መልካም እረኛ ስለመሆኑ በቃልም፥ በተግባርም፥ የመጨረሻውን ዋጋ በመክፈልም ምሳሌ የሆነ ጌታ ነው፤ ዮሐ. 10። ሁለቱም ቃላት በአዲስ ኪዳን የሚገኙና የተለመዱ ናቸው። በዚህ መጣጥፍ የ‘ፓስተር’ ቀጥተኛው ትርጉም እረኛ የሚለው ቢሆንም በተለምዶ የምንገለገልበትን መጋቢ የሚለውን እጠቀማለሁ። አሳቡ ግን እረኛ ለማለት ነው።

ከልባቸው እየተጉ የጌታን ሕዝብ እያገለገሉ የሚገኙ የተመሰገኑ ብዙ መጋቢዎች አሉ። እንዲህ ያሉ መጋቢዎች ከኖሩን የተባረክን ነን፤ እግዚአብሔር ይመስገን። ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን በመጋቢዎች አገልግሎቶች ዙሪያ በጉልህ እየታዩ ያሉ የተቃወሱ አዝማሚያዎች አሉ። በመልካም አገልጋዮች የተባረክን ጌታን እያመሰገንን የምናዝንባቸው ያሉን ደግሞ እንጸልይ። ከጸሎት በኋላ ደግሞ እንጠይቅ። ስለተቃወሱ አንዳንድ አዝማሚያዎች ከበርካታ ጥቂቶቹንና በወጉ የታዘብኳቸውን በዚህ ትንሽ መጣጥፍ በአጫጭሩ ላነሣ እወዳለሁ። እንደ ምሳሌ የጠቀስኳቸው ክስተቶች የሰዎቹንና እና የቤተ ክርስቲያን ስም አልጠቀስኩም እንጂ በትክክል የሆኑ፥ የተፈጸሙ ናቸው።

## ፩፥ ጸጋና ስጦታ

መጋቢነት ጸጋ ነው፤ ሞያ አይደለም። ሞያተኛ እረኛ ምን እንደሚያደርግ ጌታ በዮሐ. 10 አስተምሮአል። ሞያተኛ ለበጎቹ ሳይሆን ለራሱ የሚጠነቀቅ፥ ጥቅሙን የሚጠብቅና የሚያስጠብቅ ነው። መልካም እረኛ ግን በአንጻሩ ነፍሱንም ስለበጎች ይሰጣል። ነፍሱን ወዶ ከሰጠ ከነፍስ በታች ያሉትን ነገሮችማ ሳይሳሳና ሳያቅማማ የሚከፍል መሆኑ የታወቀ ነው።

በልጅነቴ ቅዳሜና እሁድ ይናፍቁኝ የነበሩ ቀናት ነበሩ። ለጥናት ወይም ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ሳይሆን ከብቶች ለመጠበቅ ከከተማው መኖሪያችን ወስደ ገጠር እርሻችን ሄጄ ስለምውል ነው። ለኔ ከብቶች ማሰማራቱ ሳይሆን ሙሉ ቀን በመስክ ላይና ውኃ ለማጠጣት ወንዝ ስንሄድ እዚያ ሲጫወቱ መዋል ነው የሚታየኝ። አንድ ቀን የሆነውን ግን ትናንት እንደሆነ ያህል አስታውሳለሁ። የሚታለቡ ላሞች ብቻ ወደ ቤት ይመጡ ነበርና እነዚያን እየነዳን በእርሻውና በከተማው መካከል ያለውን ጫካ አቋርጠን ወደ ከተማዋ ጫፍ ደረስን። ከኛ በፊት የአባቷን ከብቶች አሰማርታ የዋለች በዕድሜ የኔ እኩያ የሆነች ሹሬ የምትባል የ9 ወይ 10 ዓመት ልጅ ከብቶቿን እየነዳች ከውሎዋ ትመለሳለች። ወደ ቤቷም ቀርባ ሳለች ገላጣ ስፍራ ነበርና አንድ ትልቅ ጅብ ወጥቶ ከበጎቹ አንዷን ጭንቅላቷን ጎርሶ ሊሮጥ ሲል ሮጣ የበጓን የኋላ እግሮች ይዛ ጩኸት ጀመረች። እኛ ከኋላ፥ አባቷና አያቷ ደግሞ ድምጿን ሰምተው ከፊት መጡና እኛ እንደ ልጅነታችን ተጯጩኸን ቤተ ሰቦቿ ጅቡን ተጋፍጠው አባርረው ልጂቱም በጊቱም ተረፉ። ይህች ልጅ ለበጓ ስትል ራሷንም ከአደጋ ላይ ወርውራ ነበር። እውነተኛ እረኛ ናት!

የቤተ ክርስቲያን እረኞችም ልክ እንዲህ ሊሆኑ የተገባ ነው። በአንዳንድ ስፍራ የሚታየው ግን ራሳቸውን ዋጋ ለሚያስከፍል ሁኔታ የሚያጋፍጡ ሆነው ሳይሆን ከዚያ ለመራቅ በትጋት ሲያማትሩ ነው። በደርግ የስደት ዘመን መንጋ ጥለው ስለፈረጠጡ አገልጋዮች ከልብ እያዘኑ የእግዚአብሔርን ጠባቂነትም እያስተዋሉ ያንን ዘመን የሚያስቡ መስካሪዎችን ማድመጥ ስለ እንዲህ ያሉት ሞያተኞች ተግባራዊ ትምህርት ይሰጣል። ከልብ የሆነ ዋጋ ከፍለው ያገለገሉና እያገለገሉ ያሉ መጋቢዎች ያሉትን ያህል የነዚህ ተቃራኒ የሆኑም አሉ። እውነተኛ እረኝነት ጸጋንና ስጦታን ይጠይቃል። ጸጋ አንድ ክርስቲያን ጌታን ሲቀበል የሚቀበለው ስጦታ ነው። ጸጋ ከጌታ የምናገኘው ስጦታ ነውና በትምህርትና በልምድ የሚዳብር ቢሆንም በስልጠናና በልምምድ የሚገኝ ግን አይደለም። አንዳንድ ሰዎች ስለተማሩ ጸጋውን የተቀዳጁ እየመሰላቸው ሜዳውን የሚሮጡና መንጋውን የሚያተራምሱ አሉ። እነዚህን ማስተዋልና ራሳቸውን ራሳቸውን እንዲያዩ ማበረታታት የተገባ ነው።


© ዕዝራ ስነ ጽሑፍ 2013
ቃልህ ተገኝቶአል እኔም በልቼዋለሁ፤ አቤቱ የሠራዊት አምላክ ሆይ፥ በስምህ ተጠርቻለሁና ቃልህ ሐሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ። ኤር. ፲፭፥፲፮
ባለቤትነቱን ሳይወስዱ ማባዛትና ማደል ይፈቀዳል።

## ፪፥ ጥሪና ሸክም

ከስጦታው ወይም ከጸጋው ስጦታ ጋር አብሮ መስተዋል ያለበት ነገር ይህ ሰው ከጌታ ጥሪ አለው? የሚለው ነው። ጥሪ አንዳንዴ በአደባባይና በጉባኤም ሊከሰት ይችላል፤ ኤልያስ በእግዚአብሔር ተልኮ ኤልሳዕን ከአራሾች ጋር ሲያርስ ሳለ ነው የጠራው። ጌታ ሐዋርያቱን ከሥራ ገበታቸው ላይ (ምናልባት ሌሎችም እያዩና እየሰሙ) ነው የጠራቸው። ጳውሎስና በርናባስ ቅዱሳን አብረው ሲጸልዩ ሳሉ ጌታ ለጠራቸው ሥራ እንዲለዩ ተናገረ፤ ሐዋ. 13። ብዙውን ጊዜ ግን እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት የሚጠራቸው ጥሪውን በውስጣቸው በማስቀመጥ ነው። መብረቅም ነጎድጓድም ሳይኖር ጥሪ ይኖራል።

ጥሪ ጸጋን የሚከተል በመሆኑ ተጠራን የሚሉ ሰዎችን ጸጋው እንዳላቸው የሚያስተውሉ ዓይኖች ያሉአት ቤተ ክርስቲያን በግልጽ ታያቸዋለች። አይታም ልታሰማራቸው ይጠበቅባታል። ለአገልግሎት የሚጠራ ግን የአገልግሎቱ ጌታ ብቻ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ የአንዳንድ ሰዎችን ችሎታ አይታ ቤተ ክርስቲያን ወይም በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ የተወሰኑ ሰዎች ወይም መሪዎች ሊጠሩ ይችላሉ። የዚህ ስሕተቱ ጸጋና ችሎታን እና ችሎታንና ትምህርትን በውል መለየት ያለመቻል ነው። ሰዎች ሰዎችን ሲጠሩ ችግሩ ዘርፈ ብዙ ነው። ዋናዎቹ ከምላቸው ሁለቱ አንደኛው ብቃትና መንፈሳዊነት ያጡ ሰዎችን መሪ ሆነው በቤተ ክርስቲያን ላይ እንዲሰለጥኑ ልጓም ማስያዝና ሁለተኛው አገልጋዮቹ የሿሚዎቹን ሙቀትና ትርታ ብቻ እያደመጡ ደፋ ቀና የሚሉ መሆናቸው ነው።

አንዳንዴ ጠሪዎች ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ራሳቸው ራሳቸውን የሚጠሩና እንደናፖሊዎን በእጃቸው ዘውዳቸውን በራሳቸው ላይ የሚደፉ አሉ። እነዚህ አደገኛ ሰዎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን አጥብቃ ልትመለከታቸው የሚገባት እንዲህ ያሉትን ተኩላዎችና ቀበሮዎች ነው። እነዚህ እንደምንም ተቆናጥጠው የካሚዎኑን መሪ ከያዙ በኋላ ወደ ወደዱበት ለመሄድ እንዲያመቻቸው ራሳቸውን መተኪያ እንደሌለው ብቸኛ መሪ አድርገው የሚነድፉ ናቸው። ብቸኛው፥ ቆራጡ፥ ጀግናው፥ አብዮታዊው፥ ምኑቅጡ መሪያችን ተብሎ ሕዝብ አንድን ሰው ወድዶም፥ ፈርቶም፥ ተገድዶም፥ አምላኪ እንደሆነበት ዘመናችን በግልብጡ ይህንን በጌታም ቤት እያየን ነን። ይህ መሪን በጭፍን መከተልና ያለመጠየቅ ከጥንትም ጀምሮ ባህል ብቻ ሳይሆን ሃይማኖትም የሆነብን ነገር ነው። ንጉሥ ስዩመ እግዚአብሔር ነው ተብሎ አይጠየቅም። ጉልበተኛም መጥቶ መንግሥት ከያዘ ሌላ የባሰ ጉልበተኛ መጥቶ ግልበጣ ካልመጣ ዝም ነው። ክርስቶስን ያማከለ ሳይሆን መሪን ያጎላ ሥልጣን በክርስቶስ አካል ላይ እየተንሰራፋ አለ።

እነዚህ አንዴ አመራርን ከተቀዳጁ በኋላ ሌላውን በአውቅልሃለሁ ስሜት የበታች አድርገው፥ ወይም በምን አውቅልሃለሁ ምት ከሜዳ ውጭ አድርገው ለራሳቸው የሚኖሩ ጌታ በዮሐ. 10 ሞያተኛ ያላቸው ‘ፕሮፌሽናል እረኞች’ ናቸው። እነዚህን መሪ ብሎ በዙሪያቸው የሚጋጋ መንጋ መኖሩ ዕድሜያቸውን ያረዝመዋል። ያለጥያቄ የሚያቀርቡለትን የማይቆረጠመውን ንፍሮና የሚላሰውን ኬክ እየበላ ጥርሱ እንዲላላና እንዲሰበር ያደርጉታል። ድዳም ከሆነላቸው በኋላ ምንም አያሰጋቸው። አንዳንድ ምእመናን ችግሮች መኖራቸው የሚስተዋላቸውና ለመፍታት ሙከራ የሚያደርጉት ጊዜው በጣም ካለፈ በኋላ ነው።

ከላይ ያየናቸው አውቀው አስልተው ራሳቸውን ዙፋን ላይ የሚያኖሩ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ የራሳቸውን ድምጽ ሰምተው፥ ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን ተከትለው የእግዚአብሔር ድምጽ መስሎአቸው የሚወናበዱ ባለ ጥሪዎችም ናቸው። ደብረ ዘይት ከተማ ወንጌላዊ ሳለሁ አንድ ማታ ከአገልግሎት መልስ ሰውነቴም ደክሞ ከመተኛቴ በፊት መብራት አጥፍቼ አንድ መዝሙር እየሰማሁና ያንን እየዘመርኩ እጸልይ ነበር። በጣም ጨለማ ነው። መኖሪያዬ ከቤቱ ጀርባ በኩል ያለ ሰርቪስ ቤት ነው። ወዲያው በር ተንኳኳና፥ “ዠላለም . . . ይቺ ቡቲ ናት!” የሚል ድምጽ ስሰማ እንዴት ተስፈንጥሬ ተነስቼ መብራቱን አብርቼ በሩንም በርግጄ እንደከፈትኩትና እንደወጣሁ አሁንም ይገርመኛል። ከፍቼ ሳይ እውጪ ድምጹን የሰማሁት ቢኒ የለም፤ ቢኒ ብቻ ሳይሆን ማንም የለም። በዚህ ጨለማ የዚህን ልጅ ድምጽ የሰማሁት ምን ሊያደርግ መጥቶ ነው ብዬ፥ ስወጣም ማንም ስለሌለ ማመን ስላልቻልኩ እቤቱ ሄጄ (ሦስት ቤቶች አንድ ላይ ያሉበት ትልቅ ግቢ ነው) አንኳኳሁና ቢኒ እቤት እንደሆነ ጠየቅኩ። መኖሩን አረጋግጠው ምን እንደሆነ ሲጠይቁኝ፥ “አአይ ድምጽ የሰማሁ መስሎኝ ነው” ብዬ ተመለስኩ። ሳይገርማቸው አልቀረም። ኋላ ነገሩ ሲገባኝ በራሴ ለረጅም ጊዜና ብቻዬን ብሆንም ድምጼን እያሰማሁ ነበር የሳቅኩት። የሆነው ይህ ነው፤ ቀን ለመዘምራን የማለማምደውን መዝሙር በግድ ጊታር (መጫወት ስለማልችል ‘የግድ ጊታር’ ነበር የምላት) እየተጫወትኩ እቀርጽ ነበር፤ ሕጻናት ልጆች ውጪ ይጫወታሉ። በር ተንኳኳና ከልጆቹ አንዱ፥ ቢኒ “ዠላለም . . . ይቺ ቡቲ ናት!” አለ። በሩን ያንኳኳው እርሱ አለመሆኑን መናገሩ ነው። እኔ መዘመሬን ቀጥዬ ዝም ስል ራቅ ብለው ጨዋታቸውን ቀጠሉ። ቤቷ በጣም ጠባብ ነበረችና መቅረጫው እበሩ አጠገብ ስለነበረ ከኔ ድምጽ በላይ ጎልቶ የቢኒ ድምጽ ነበረ የተሰማው። እና የሰማሁት ያድድ የተቀረጸ ድምጽ ነበር። ግን የተቀረጸ ሳይሆን በዚያ ጨለማ የእውን ድምጽ የሰማሁ መስሎኝ ነው በሰከንድ ውስጥ ራሴን ከበር ውጪ ያገኘሁት።

አንዳንድ አገልጋዮች የሚሰሙት ድምጽ እንደዚህ ያለ ሳይሆን አይቀርም። በውስጣቸው የሚመላለስ የራሳቸው ድምጽ ተደጋግሞ ሲሰማቸው ራሳቸውን አደባባይ ላይ ያገኙታል። ስለ መጋቢዎች አባዜ ቢሆንም የምጽፈው ጥሪ ያላቸው ሰዎች እርግጠኛ ይሆኑ ዘንድ ማሳሰብም ተገቢ ይመስለኛል። ያለጥሪ አገልግሎትን የሚጀምሩ እነዚህ በሰውኛ ጉልበት ይሮጡና አገልግሎት ዳገት ሲሆንባቸው የሚለግሙ፥ የመውረጃ ፌርማታ እስኪደርሱ እንኳ የማይታገሱ ናቸው። ጳውሎስ በ2ቆሮ. 11፥28 *የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው* አለ። ይህን ያለው የደረሰበትን ሁሉ ዘርዝሮ የቀረውን ሳይቆጥር ነው። ይህንን የሚለው ሐዋርያነቱን ለናቁ የቆሮንቶስ ሰዎች ነው። እውነተኛ ጥሪ ባለበት ቢከብድም እንኳ አገልግሎትን መሸከም የሚችል የፈረጠመ ትከሻ ከእግዚአብሔር ዘንድ አለ። ቤተ ክርስቲያን የሌላቸውና ከተጠያቂነት የራቁ ሰዎች ኮንፍራንስ ላይ እንዲናገሩ ከተጠሩ ያንን እንደ ጥሪ የሚቆጥሩ ሰዎች አሉ። ይህ ግብዣ ነው። ግብዣና ጥሪ የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

አንዳንዶች ደግሞ መጠራታቸውን ሰምተው ግን ከዚያ የሚቀጥለውን በውል ሳይሰሙ ጉዞ ይጀምራሉ። የትም እየሄዱ እንዳልሆነ የሚገባቸው መንገዱን ካጋመሱ በኋላ ነው። አንድ ጓደና አለኝ፤ በጣም ፈጣን ወይም በጣም ችኩል። አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያናቸው ግቢ ይጫወታል። በዚያው ጊዜ ደግሞ አንድ ወንጌላዊ ክርስቲያኖችን ያስተምራል። ስለሚያስተምረው ነገር ምሳሌ እንዲሆን ብሎ ይህንን ችኩል ልጅ

ጠራው። ልጁም በችኩል እግሩ እየሮጠ መጣ። ወደ አንድ ቦታ እያመለከተ፥ “ሂድና . . .” ከማለቱ ተንደርድሮ ወዳሳየው ቦታ መሮጥ ጀመረ። ወንጌላዊው ያለው፥ “ሂድና ሙት” ነበር። ልጁ ያሰበው እንደለመደው ‘ሂድና ይህን አምጣ ወይም ያንን አድርግ’ ይለኛል ብሎ ነው። ይፍጠንና ጉዞ ይጀምር እንጂ የተባለውን ግን ሰምቷል። መስማቱን ያወቀውና ጥያቄ የሆነበት እየሄደ መንገድ ላይ ቆሞ፥ “ሂድና ምን?” ብሎ ሲያረጋግጥ ነው። ወንጌላዊው ሊያስተምርበት የፈለገውን ነገር አግኝቶ ነበር። አንዳንድ አገልጋዮች ደግሞ እንደዚህ ናቸው። ተጠርተዋል፤ ግን አይጠይቁም።

ለአገልግሎት በውስጤ ጥሪ የተሰማኝ ገና ጌታን ባወቅኩ በ2ኛ ዓመቴ ላይ ነበር። የዩኒቨርሲቲ ሁለተኛ ዓመት ተማሪ ነበርኩ። በውስጤ ጎልቶና ደጋግሞ የሚሰማኝ ወንጌልን ማስተማርና ገና በዚያን ጊዜ እያስተዋልኩ ያለኋቸው የተሳሳቱ ትምህርቶችን ስሕተት መግለጥ ነበረ። ግን በቂ የሆነ እውቀትና ትምህርት አልነበረኝም። እንደተሰማኝ ትምህርቴን አቋርጬ አንድ ገጠር፥ ምናልባት እስላሞች የሚበዙበት ወይም ገዳም ያለበት አካባቢ ሄዶ ያገኙትን እየበሉ መኖርና ማስተማር ብቻ ነበር የሚታየኝ። ይህ ነገር በውስጤ እየጎላ ሲመጣ ከሰምይ ድምጽ መጠበቅ እንደሌልለብኝ ገብቶኛልና ወደ ጋሽ አብርሃም ደብዳቤ ጻፍኩ። መጋቢ አብርሃም ዮሴፍ (ጋሽ አብርሃም ነው የምንለው) በመጀመሪያ የክርስትና ወራቶቼ የጌታን ቃል የመገበኝና ያስተማረኝ የኅብረት አምባ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ነበረ። እኔ አስመራ እርሱ አዲስ አበባ ነው የነበርነው። በጣም አበረታትቶኝ፥ እንደሚጸልይ ቃል ገብቶልኝ፥ ስንገናኝ ብዙ እንደናወራና አብረን እንደምንጸልይም ነግሮኝ ግን ትምህርቴን እንዳላቋርጥና እንድቀጥል ነግሮኝ ትምህርቴን ቀጠልኩና ጨረስኩ። ያ ምክርና ጸሎት እጅግ ረዳኝ፤ ጌታም ያን ጸሎትና ምክር ሰምቶ ነበር። መቆየቴም ብዙ ጠቀመኝ። የጌታ በሆነው ነገር በሰልኩበት። አገልግሎትን፥ ሰልፍና ዘመቻንም ለመድኩ። ጥሪዬም አልጠነዛም። ትምህርቴን ጨርሼ እንደጨረስኩ በተገቢውና በአስፈላጊው ጊዜ ጌታ ወደመራኝ ስፍራ መራኝ። ጥሪ ከኖረ የቅዱሳን ጸሎትና ምክር ይጠቅም እንጂ አይጎዳም። ጥሪ ከኖረ ከየአቅጣጫው ማረጋገጥ ተገቢ ነው። ከበሰሉ አስተማሪዎቻችንና ከመሪዎችም ጋር መምከር ብስለት እንጂ ብክነት አይደለም።

ጳውሎስ ከተጠራ በኋላ ማንነቱን ወዲያው ነው የገለጠው። መለወጡን፥ የጌታ መሆኑን በግልጥ አሳየ። ግን ወዲያው ወደተጠራለት ወደ አሕዛብ አስተማሪነቱ አልተሰማራም። ከጠሪው ጋር ጊዜ ወሰደ። ስለዚህ ነገር ለገላትያ ሰዎች ሲናገር በገላ. 1፥15-18 እንዲህ አለ፥ *ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም። ከእኔም በፊት ሐዋርያት ወደ ነበሩት ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም፥ ነገር ግን ወደ ዓረብ አገር ሄድሁ እንደ ገናም ወደ ደማስቆ ተመለስሁ። ከዚህ ወዲያ ከሦስት ዓመት በኋላ ኬፋን ልጠይቅ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቼ ከእርሱ ጋር አሥራ አምስት ቀን ሰነበትሁ።* አገልጋይ ጥሪውን ሲያስተውል ጠሪውን ያከብራል፤ ከጠሪው ጋር በቂ ጊዜ ያጠፋል። ሽክሙ ከሆነም እንደ ይሳኮር አጥንተ ብርቱ አህያ መሆን ደስታው ነው። ስለ በቂ ጊዜ አንድ ነገር ልበል። በቅርብ አንድ አገልጋይ አገልግሎን ነበርና እንደ ጸሎት ርእስ አድርጎ በቀጣዮቹ ሁለት ወራት የሚሄድባቸውንና የሚያገለግልባቸውን ቦታዎች በዝርዝር ነገረን። አገላለጡ የማንነቱ ማስተዋወቂያም ሆኖ ነው የቀረበው። ወደ 8 ወይ 9 የተለያዩ ግዛቶችና አገሮች እየዞረ ቢያንስ በእያንዳንዱ ከ2 እስከ 4 ቀናት ስለሚያገለግል በምን ጊዜ ዝግጅት ያንን ሕዝብ እንደሚመግብ ጥያቄ ሆነብኝ። ሲመጣ እንዲያስተምር የሚጠበቅበትን ርእስ ትቶ ፈጽሞ ሌላ ነገር ስላስተማረ በዝግጅት የተሰናዳ ሳይሆን የከለሳና የሸምደዳ ነገር የሚያደርግ መሆኑ ይታይ ነበርና ያንን የሚመስል በቦታዎቹ ሁሉ እንደሚደረግ ለመረዳት አልከበደኝም።

## ፫፥ ትምህርትና ስልጠና

መጋቢ መጋቢ ነውና የሚመግበው ሊኖረው የግድ ነው። ምግቡ ደግሞ የማያልቀው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ራሱ ቃሉን እንደ ምግቡ የሚበላ መሆን አለበት ማለት ነው። ቃሉን ከቃሉ ጌታ መማር ውብ ነው። ቃሉን መርቶ፥ ነድቶ ካስጻፈው መንፈስ ከመንፈስ ቅዱስ መማር ድንቅ ነው። ነገር ግን መንፈሳዊ፥ ክርስቲያናዊ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ መማር ሲችል ያልተማረ ሰው መጋቢ ሊሆን መድፈር የለበትም።

የመማር ‘ዕድል’ ማጣት አንድ ነገር ነው። ፍላጎቱ ካለ ግን በሩ ብዙ ነው። ዛሬ ከገዛ ቤት ሳይወጡም መማር ይቻላል። ከጥቂት ዓመታት በፊት ከአንድ መጋቢ ጋር ተዋወቅን። አዲስ መጋቢ ሆኖ ተጠርቶ ገና መምጣቱ ነበር። ስንተዋወቅ አንድ የታወቀ ሴሚነሪ ጠራልኝና ከዚያ በማስተርስ እንደተመረቀ ነገረኝ። የጠራችው ቤተ ክርስቲያንም ያንን ነው የምታውቀው። ቤተ ክርስቲያን በቀላሉ አማኝ አይደለች? ማስረጃውን አልጠየቀችውም፤ ዝርዝር ምስክርነቱንም አልሰማችም፤ ሌላ ምስክርም አልፈለገችም። ቆይቶ ነው የሚያስተምረውም እየነጠፈ ሲመጣና የተደራረቡ ችግሮችም ሲፈጠሩ የትምህርትን (የመማርን) ጥያቄ ራሱ ሲያነሳ ያልተማረ መሆኑን ያሳወቀውና የታወቀው። አለመማር ነውር አይደለም፤ ያልሆኑትን የተማሩ መምሰል ግን ነው።

አገልጋይ ስለተማረ ብቻ ብቁ ሆኗል ማለትም አይደለም። ስላልተማረ ብቻም ከጸጋው ጎድሎአል ማለትም አይደለም። ይህ መዘንጋት የሌለበት ነገር ነው። ትምህርት ጸጋን ያቀልማል እንጂ የጸጋና የጥሪ ልዋጭ አይደለም። ትምህርትን መጥላት ግን የአገልጋይ መታወቂያ መሆን የለበትም። በሐዋ. 4፥13 የአይሁድ ሊቃውንት እነ ጴጥሮስን “ያልተማሩ እንደሆኑ አስተውለው አደነቁ” ተብሎ ተጽፎአል። በእነርሱ ትምህርት ቤትና ሥርዓተ ትምህርት አይማሩ እንጂ እነ ጴጥሮስስ የተማሩ ነበሩ። የእግዚአብሔር አንድያ ልጁ ያስተማራቸው ነበሩ። ይህንን አባባል አንዳንድ አገልጋዮች መገበዣና ያለመማራቸው መሸፈኛ ያደርጉታል። ይህ ስሕተት ነው። አገልጋይ ሁሉ የላቀ ትምህርት እስኪቀበል ብንጠብቅ አገልጋይ አናገኝም። ትምህርትን የሚንቅ አገልጋይ ሲያገለግል ደግሞ ስሕተቶች ይፈለፈላሉ።

እውነተኛ አገልጋይ ተማሪ ብቻ ሳይሆን የእድሜ ልክ ተማሪ ነው። ይበልጥ በተማረ ልክ ብዙ እንደሚቀረው ደግሞ ያውቃል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መግባት ባይችል የእግዚአብሔርን ቃል በስርዓት ለማጥናት እንዲችል ትጉህ አንባቢ መሆን ይጠበቅበታል። የማንበብ ልማድ በሕዝባችን በአጠቃላይና በተለይ በክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ ዘንድ ያልዳበረ ብቻ ሳይሆን እስኪያሳፍር የመነመነ ነው። አንባቢ ካለመሆንና ቃሉን በስርዓት ካለመማር የተነሣ በኩረጃ ብቻ የሚያገለግሉ ብዙ መጋቢዎች አሉ። የአንዳንዶቹ አኮራረጅ ቃል በቃል ትምህርቱን ብቻ ሳይሆን የሰውነትና የአለባበስ፥ የድምጸትና የእጅ አወረጫጨትም ጭምር ነው። የተሳሳተ ትምህርት እየጎረሱ እያገሱ፥ እንደ ገደል ማሚቶና እንደ በቀቀን እየደገሙ ስሕተቶችን በኮፒ እያባዙና እየነዙ የስሕተት መሣሪያ

የሆኑ መጋቢዎች ጥቂቶች አይደሉም። እንዲህ የሚያደርጉቱን አገልጋዮች ስናጤን መሠረታዊው ችግር አለመማራቸው ሆኖ እናገኘዋለን። የቤተ ክርስቲያናችን መተዳደሪያ ደንብ ሲቀረጽ መጋቢ ተደርጎ የሚሾም ሰው ቢሆን ቢሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ የተማረ፥ ካልሆነ ደግሞ ለአገልግሎት ከተሾመ በኋላ ለመማር የማያቅማማ መሆን እንዳለበት አስቀምጠናል። ቃሉን የሚመግብ መጋቢ ቃሉን የሚመገብ፥ የሚማርና የሚመረምር ሊሆን ግድ ነው፤ 1ጢሞ. 4፥6።

አንድ ጓደኛዬ ባለበት ቤተ ክርስቲያን በአጋጣሚ በተደዋወልን ቁጥር ኮንፍራንስ ላይ እንደቆዩ ይነግረኛል። ሁሌ እንደዚያ ስለሚል አንድ ቀን የምናወራውን አቁሜ በግልጽ ጠየቅኩት። ስናወራ ከነበርንበት ሳምንት በፊት ባሉት 3 ወራት (12 እሁዶች) 9 ወይ 10ሩ ኮንፍራንስ የተደረገባቸው ናቸው። “ምነው መጋቢውስ?” አልኩት። “አሁንማ ሕዝቡ ኮንፍራንስ ስለለመደ የሱ ነገር አይጥመውም፤ እሱም እነሱን ለመያዝ ይህንን ነገር ዘዴ ያደረገ ይመስለኛል” አለኝ። ስለ ትምህርቱ ስጠይቀው፥ “አይይ እሱ ቢኖረውማ ጥሩ ነበር፤ እሱኮ የልምድ አገልጋይ ነው” አለኝ። የዚህ መጋቢ ሥራ እየደገሱ መጋበዝ ብቻ ነው ማለት ነው። ድግስ እያሸተቱ የሚዞሩ ጩሉሌዎች ደግሞ ብዛታቸው!

## ፬፥ ማንነትና የማንነት

ማንነትና ባህርይ የተያያዙ ናቸው። ማንነት ውስጣዊ እኛነት ሲሆን ባህርይ ያ ውስጣዊ ማንነታችን ለሌሎች የሚታይበት ጠባያችን ነው። የማንነት ደግሞ ሌላው የማንነታችን አስተዋዋቂ ነው። የማንነት ደግሞ ለማን የመኖራችን ገላጭ ነው። የባለቤትነት ጥያቄ ነው። በቀላል አገላለጥ መጋቢው ወይም አገልጋዩ የራሱ ሰው ነው? ወይስ የሰው ሰው ነው? ወይስ የእግዚአብሔር ሰው ነው? የሚለው ጥያቄ የሚመለስበት ነው።

አገልጋይ የአንዱ የእግዚአብሔር አሳብ አገልጋይ ካልሆነ የራሱ ፈቃድ አገልጋይ ይሆናል። የሰው ሰው ወይም ሌሎችን ለማስደሰት የሚጥር ከሆነም ዞሮ ዞሮ ሌሎችን ባለማስቀየም የራሱን ምቾት ለመጠበቅና ለማስጠበቅ መቆሙ ነው። ከዚህ በፊት በሦስት የዕዝራ ስርጭቶች *የሕዝብ ሰው* በሚል ርዕስ ይህንን አሳብ በጥልቀት ተመልክተን ነበር። የሕዝብ ሰዎች ከሆኑት መካከል ጉልህ ናሙና የሚሆኑትን ሳኦልን ሰሎሞንን እና ጲላጦስን በዝርዝር አይተን ነበር። እነዚህ ሰዎች ዘመናቸውን ሁሉ የሰዎችን ፍላጎት ለማገልገል ታጥቀው ተጠንቅቀው የቆሙ ነበሩ። ሰዎችን ማስደሰታቸው ለሰዎች ይመስላል እንጂ የመጨረሻ ግቡ ለራሳቸው የመቆማቸው ምልክት ነው።

መጋቢዎች ወደዚህ ወጥመድ ውስጥ በቀላሉ የሚገቡ ሰዎች ናቸው። ከላይ ከተጠቀሱት የጸጋና ስጦታ፥ የጥሪና ሸክም፥ ወይም የትምህርት ጉድለት የተነሣ ድጋፍ የመፈለግና ይህ ድጋፍ ደግሞ ጤናማ ካልሆነ ያንን ድጋፍ ለማስደሰት ሲባል የሚወድቁበት ማጥ ነው። ‘እነ እገሌን አስቀይም ይሆን? እነ እገሊትን አስቆጣ ይሆን’ በሚል ጥያቄ የታጠረ ስብከትና ትምህርት ወደ ጎል እየታለመ ወደ ውጪ እንደምትመታ ኳስ ማለት ነው። የራስ ወይም የሌላ አስደሳች ለመሆን ሲጣር ወደ ሌላ ክርስቶስና ወደ ሌላ ወንጌል ድጥ በቀላሉ ሊወደቅ ይቻላል።

አንድ ጊዜ አንድ ክርስቲያን ባደገበት ቤተ ክርስቲያን ልማድ ሕጻን ልጁን ማስጠመቅ ፈለገና መጋቢውን አማከረው። መጋቢውም፥ “ምን ችግር አለ? አጠምቅልሃለሁ” ብሎ በእሁድ አምልኮ ሳይሆን በሌላ ቀን በተደረገ ዝግጅት አጠመቀለት። ሌላ መጋቢ ደግሞ ከሕጻን አጥማቂ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ ሳለ አምኖበት ሳይሆን የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ስለሆነ ብቻ ያመኑትን ያጠምቃል። ይህ የእምነት አቋምን የሚገዳደር እርምጃ ቢሆንም አብሮት የተጠመደው ችግር ሰዎችን ቅር ያለማሰኘት ጣጣ፥ ሰውን የመፍራት ወጥመድ ነው፤ ምሳ. 29፥25።

እንደዚህ ነው የወንጌሉን ክርስቶስን ሳይሆን ሰዎች የራሳቸውን ክርስቶስ እየፈጠሩ የሚሰብኩት። ይህ ሌላ ወንጌል ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ሌላ ክርስቶስና ልዩ ወንጌል ወደተቀበሉ የገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ሲጽፍ የሰዎች አስደሳች ስላለመሆኑ እንዲህ አለ፥ *ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም፥* ገላ. 1፥10። የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔር ሲደሰት ይደሰታሉ፤ ወይም እግዚአብሔርን የሚያስደስት ማናቸውም ነገር ያስደስታቸዋል። የጌታ ደስታ ኃይላቸው የማይሆን ሰዎችን ለማስደሰት መጣር ከንቱ ልፋት ብቻ ሳይሆን ትልቅ መፍረስም ነው። ደግሞም ሰዎችን የጌታ ደስታ ካላስደሰታቸው በምንም ነገር ልናስደስታቸው መጣር የለብንም። የጌታ ወዳጆች አይደሉማ! እነዚህን ማስደሰት አያሻም።

## ፭፥ ስምሪት፥ አስተዳደርና ግንኙነት

ይህ በተለይ በምዕራቡ ዓለም በአመዛኙ የሚታየው የመጋቢያዊ (Pastoral / Episcopalian) አስተዳደርን ችግር ይመለከታል። አሁን አሁን ጥያቄ እየፈጠረ እየመጣ ያለው የአንድ ሰው ብቻ አስተዳደር የገነነበት አሠራር የሚፈጥረው ችግር መዘዘ ብዙ እየሆነ መጥቶአል።

በምዕራቧ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና አስተዳደር ሙያዊ መልክ እየያዘ መጥቷል። የአበሻዎቹ አብያተ ክርስቲያናትና የኛዎቹ መጋቢዎችም መጀመሪያ የመጡቱ በዚያ መስመር ስለሄዱ ይመስላል አብላጫዎቹ ያንን ቦይ ተከትለው መፍሰስ ቀጠሉ። መጋቢው አስተማሪውና አስተዳዳሪው፥ ግምጃ ቤቱና ባንክ ቤቱ፥ ሿሚና ሻሪው፥ አፍላቂና አድራጊው፥ ተፋላሚና ተሸላሚው እርሱ ብቻ የሆነበት ሁኔታ ታየ።

መጋቢው እየተሳተፈ አሳታፊና እየተሰማራ አሰማሪ ነው? ወይስ ተቆጣጣሪና አዛዥ ብቻ ነው? የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ስልቶች መኖራቸውና እነዚህም የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳሏቸው የታወቀ ነው። ሰው ሳይኖርና ቤተ ክርስቲያን ሲቆረቆር አንዱ ሰው ብዙ መለዮ ቢለብስ ትክክል ነው። ሰው ሳይታጣ አንዱ ብቻ ሁሉን በሚሆንበት ስፍራ ግን ሁሌም ችግር አለ። አምባ ገነንነት፥ ፈላጭ ቆራጭነት፥ የመጋቢ በላይነት፥ ምግባረ ብልሹነት፥ ንዋይ መዝባሪነት፥ የስሕተት ትምህርት መንገድ መንጣሪነት ተግተልትለው ይመጣሉ። አርቀው የሚያዩ፥ የዘመኑ መልክና ችግር የሚስተዋላቸው፥ አካባቢያቸውን በወንጌል ለመድረስ በእምነት የሚራመዱ መሪዎች መኖራቸው እሙን ነው። መሪ የሆኑ መሪዎች መኖራቸው ሐቅ ነው። ጌታም ከጸጋ ስጦታዎች አገዛዝን ማድረጉ በቃሉ የተጻፈ ነው። እነዚህ ግን ይህንን ማጋራትና አብረው መሄድ እየቻሉ ‘ባለ ራዕይ’ የሚል ቆብ ደፍተው ብቻቸውን እንጣጥ ብለው መሄድም የለባቸውም። ብልት አንድ ብልት እንጂ አካልን በሙሉ ልሁን ካለ ችግር ነው።

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዘአካል (organism) ብቻ ሳትሆን ድርጅትም (organization) ጭምር ናትና በጥንቃቄ ጊዜ ተወስዶበት በስፍራው የተሰናዳና የተቀመጠ የእምነት አንቀጽና አቋም፥ የመተዳደሪያ ደንብና የአሠራር መመሪያ ያስፈልጋታል። አንድ ጊዜ የተወሰነ ጊዜ በቆየሁባት

ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን መተዳደሪያ ደንባቸውን ስጠይቅ የነገሩኝ በድረ ገጻቸው ላይ መኖሩን ነበር። እንዴት ጠቅላላውን ደንብ ድረ ገጹ ላይ አኖሩት ብዬ ገጹን ሳየው ወደ 10 የሚደርሱ በጥቂት መስመሮች የተጻፈ የእምነት መግለጫ ብቻ ነው። ይህንን ማየቴንና ግን ደንቡን ለማወቅ መፈለጌን ነግሬ ስጠይቅ ያለው ያ ብቻ መሆኑን ነገሩኝ። ይህ የደንብ አለመኖር ችግር ምንም ግድ ለማይሰማቸው ምንም ላይመስል ይችላል። ሲያስፈልግ ወይም በሚያስፈልግበት ጊዜ ግን ደንብ ተንደፋድፈው የሚሠሩት ነገር አለመሆኑ መታወቅ አለበት። አንዴ በአባላት ስብሰባ ላይ ደንቡን እንዲያቀርብ ተጠይቆ እንዲህ ያደረገ፥ ወደ 20 ገጽ ያህል ጠቅላላ መተዳደሪያ ደንብ በአንድ ሌሊት በጭንቅ ሠርቶ ለስብሰባ ያቀረበ መጋቢ አውቃለሁ። ግን ውጤቱ ጥሩ አልነበረም። የአንድ ሰው ብቻ ሥራና ሳይሆን ሳይከካ የተቦካ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ራሱን ጠጋግኖ በቦታው ለመጠበቅ ያደረገው ሙከራ ምሆኑም ጭምር ነው።

አንዳንድ መጋቢዎች ለራሳቸው የሚመች ደንብ ሠርተው በቦርሳቸው ስለሚሄዱ ከነባሩ ደንብ ጋር ግንባር ለግንባር መጋጨት ይጠብቃቸዋል። ከዚህ በፊት በነበርኩባት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ስትመሠረት ያዘጋጀነው ደንብ ነበረን። ከዓመታት በኋላ መጋቢ ሲመጣ ደንቡን አይቶታል፤ አልወደደውም፤ አለመውደዱን ግን ለአንድ ሁለቱ መሪዎች ብቻ እንጂ ለጉባኤው ወይም ለጠቅላላ ሽማግሌዎች ሳይነግር እንደተቀበለ ሆኖ ወይም መስሎ አገልግሎት ጀመረ። ያዋያቸው ሰዎች ደግሞ እንደሚወደው ተደርጎ እንደሚለወጥለት ተስፋ ሰጥተውት ይህ ተስፋ ሳይሆን ብዙ ዘገየ። የተባለው እንደማይሆን ተረድቶ አንድ ቀን የራሱን ደንብ አትሞ ለጉባኤው አደለ። በቀድሞው ደንብ ግን ደንቡን ማንም አንድ ሰው ብቻውን ጠቅላላውን መለወጥ ቀርቶ ጥቂቱንም ማሻሻል አለመቻሉ በግልጽ እንደተጻፈ አላስተዋለም። ወይም ደንታ አልሰጠውም። ይህ ሰው በጻፈው ደንብ መሠረት ለምንም አካል፥ ለሽማግሌዎች ጉባኤም ለጠቅላላ ጉባኤም ተጠያቂ መሆንን አልፈለገም። ከዚያ የጀመረው ግጭት መረረና መጋቢው መንጋውን ጥሎ የተወሰኑትን ይዞ ወጥቶ ሌላ ማህበር መስርቶ ቀጠለ። አስተዳደራዊና ግንኙነታዊ መስመር በግልጽ ካልተሰመረ ውሎ አድሮ በመጋቢ አገልግሎትና በምገባ ሂደት ችግር ሳይፈጠር አይቀርም። ጉባኤ የሚያውቀውና የተቀበለው ደንብ ታውቆ ተቀርጾ እንጂ ጉባኤ የማያውቀው ደንብ በአንድ ሰው ተደርሶ እንደ ቀንበር በጫንቃ ላይ መደረግ የለበትም።

## ፮፥ መንጋ አልባ እረኞች

ስለ እረኛ አልባ መንጋዎች መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል፤ ዘኍ. 27፥16-17፤ ሕዝ. 34፥5፤ ዘካ. 10፥2፤ ማቴ. 9፥36፤ ማር. 6፥34። ስለ መንጋ አልባ እረኛዎች ደግሞ መጀመሪያ ጽፎ ያነበብኩት ጳውሎስ ፍቃዱ ነው።[1] የመንጋ አልባ እረኞች መኖር እውነት ነው። የዛሬ 4 ዓመት የዕዝራን ስርጭት ስጀምር በመጀመሪያው ቁጥር ስለ እረኖች ከ1ጴጥ. 5፥1-4 ሳካፍል ይህንን አሳብ በመጠኑ አንሥቼ ነበር። ከጻፍኩት ቀንጨብ አድርጌ ለመጥቀስ፥ *ዛሬ በዓለማችን ቤተ ክርስቲያን በአደገኛ ሁኔታ አሳሳቢ እየሆነ የመጣው ጉዳይ እረኛ የሌላቸው መንጋዎች እና መንጋ የሌላቸው "እረኞች" እየበዙ መምጣት ነው። ምእመናን ወይም መንጋ ሆነው እረኛ ከሌላቸው ችግሩ ከሁለቱም አቅጣጫ ሊሆን ይችላል። ወይ መንጋው አፈንጋጭ ነው፤ ወይም እረኛው ታካችና ሐኬተኛ ወይም ፈጽሞ ግድ የሌለው ደንታቢስ ነው። "እረኛ" ተብሎ መንጋ ከሌለው ደግሞ ወይ ያለቦታው ነው፤ ወይም ያለጥሪና ያለ ስጦታው ነው። እነዚህ መንጋ-የለሽ እረኞች የመኖራቸው ምክንያቱ ብዙ ነው፤ ሥራ መጥላትና ስንፍና፥ የተሰማሩበትና የሞከሩት መስክ አልሳካ ሲል ማምለጫ፥ ገንዘብና ዝና በአቋራጭ ለማግኘት መነገጃ፥ በቀላሉ የሚያምኑና የሚታለሉ ሰዎችን መጠቀሚያ የማድረግ ዝንባሌ፥ የሌሎች ግፊትና ጫና፥ ከእግዚአብሔር ያልሆነ የጥሪ ስሜት ጥቂቶቹ ምክንያቶች ናቸው* ብዬ ነበር። ዛሬም ተጠሪነት የሌላቸው ተባራሪ መጋቢዎች ከትናንት ይልቅ በዝተዋል። አንድ ጓደኛዬ በሚኖርባት ከተማ ያሉት 'መጋቢዎች' ብዛትና የምእመናን ቁጥር 1 ለ 12 እንደደረሰ አስልቷል። እነርሱ እንደ ኢየሱስ ጉባኤው እንደ ሐዋርያት እየሆኑ ይሆን?

ይህ በብዙ ከተማዎች የሚታይ ችግር ነው። አገር ቤትም፥ አገር ውጪም። ትንሽ ችግር ስትነሣ ያቺን ለመፍታት መነጋገሪያ መድረክ የለም። አንዳንዱ ለመጠየቅ ይፈራል። ሌላው ያድማል። ተጠያቂው መጠየቅ አይፈልግም። ደንቡም በቦታው የለም። ደንቡና ስርዓቱ በስፍራው ኖሮ ቢሆን ችግር አይኖርም ማለት ሳይሆን ከችግሮቹ ብዙዎቹ መወያያ እስኪሆኑ ባልደረሱም ነበር። እና አኩራፊው ይወጣል። አጋጣሚዋን ተከትሎ እዚያ ሥልጣን ኮርቻ ላይ ቂብ ሊል የሚፈልገው የሚወድቅበትን መነዝነዝ ይጀምራል። ምናልባት ከመጋረጃ ጀርባ ጠንሳሽና ጠማቂው ራሱም ሊሆን ይችላል። እና አዲስ ጉባኤ ይከፈትና ይጀመራል። ይህ እንዲህ እያለ ይቀጥላል። ያልዳኑ እየሰሙና እየታዘቡ ለምስክርነት በር እስከሚዘጋ ድረስ ችግር ፈጠረ። አንዳንዱ መኖሪያው እያደረገው ያለ ሙያ ሆኗል መጋቢነት። አንዳንዱ ተዘዋዋሪ መጋቢ ሲጠሩት ብቻ የሚሄድና ምንም መንጋም ሆነ ቤተ ክርስቲያን የሌለው ነው። የተጠራ ሳይሆን የተጋበዘ አገልጋይ ማለት ነው። ግብዣ ጥሪ ያለመሆኑን አይተናል።

መንጋ እረኛ ሲያጣ ለአደጋ ይጋለጣል። እረኛ መንጋ ሲያጣ ደግሞ አውደልዳይ መሆን ነው። ከላይ የጠቀስኩት ጳውሎስ ፍቃዱ መንጋ የለሽ እረኞች ያላቸውን ከጠቀሰባቸው ሐረጎች ጥቂቶቹ፥ የስደት ፓስተሮች (ልክ አገርና ሕዝብ እንደሌላቸው ንጉሦች)፥ አየር ባየር ፓስተሮች፥ እነርሱ ስለሚሰብኩት ስብከታቸው ሰሚው በእነርሱ ፈንታ የሚሸማቀቅላቸው፥ የሕዝብ ስሜት ወይም "ሙድ" ተከታዮች፥ የልምድ አዋላጆች፥ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ማራቶን አንከራታቾች፥ ያልበላበት የሚያከኩ አካኪዎች፥ የምስባክ (ፑልፒት) አንበሳዎች፥ የትምህርት ናቂዎችና ስነ መለኮትን "የተቆላ ዘር" ባዮች፥ የኮንፈረንስ ማስታወቂያና የመጽሔት ሽፋን አፈንፋኞች የሚሉ ይገኙባቸዋል። እነዚህ ቃላት መንጋ የለሽ መጋቢዎቻችንን በጥቅሉ በእርግጥ ይገልጣሉ። መንጋው በአካል ላይኖር ብቻ ሳይሆን ሊኖርም ይችልና መንጋው ኖሮ የእረኛው ልብ ግን ሌላ ስፍራ ከሆነ ይህም ተመሳሳይ ችግር ነው። ይህም የሚታይ፥ ግን የሚያሳዝን እውነት ነው።

## ፯፥ ፈተናና ወጥመዶች

መጋቢዎች የሚጠላለፉባቸው በርካታ ፈተናዎችና ወጥመዶች ብዙ ናቸው። አንዳንዶቹ አሳቦች የተደገሙና ከላይ በጎንዮሽ የተነኩ ቢሆኑም ዋና የመሰሉኝን ጥቂቶቹን ከታች እናያለን።

---

1 *ማቴቴስ፥ ግንቦት 2000።*

## ማዕረግና ሹመት

ለምን የእንግሊዝኛውን ወይም የሮማይስጡን ፓስተር የሚል ቃል እንደምንጠቀምና ለአገራችን መጋቢዎች የዚህ ጅማሬም ምን መሆኑን አላውቅም። ምናልባት የመጀመሪያዎቹ መጋቢዎች ከተሜዎች ስለሆኑና እረኛ ደግሞ ከስድብ የማይተናነስ ገጠሬነት ስለሆነ ሳይሆን አይቀርም ፓስተር የምትባለው ስያሜ የተወደደችው። አንዳንዶች አጥብቀው የሚወዷት ከኃላፊነቷ ይልቅ ሥልጣኗንና [ሥልጣን አለመሆኑ ሳይገባቸው] ማዕረጓን ነው። የሚፈልጓት ስያሜ ናት። አሁን ሐዋርያና ነቢይ የሚባሉም ተጨምረዋል። ኤጲስ ቆጶስና ጳጳስም መንገድ ላይ ሳይሆኑ አይቀሩም። አንዳንዶቹ የፈረንጅኛውን Reverend ከስማቸው በፊት ይከትቡ ጀምረዋል። ስማቸውን በአማርኛ ሲጽፉ ምን እንደሚሉት አላየሁም። ምናልባት እንደ ፓስተር ራሱን እንግሊዝኛውን በመጠቀም ሬቨረንድ ሳይባሉ አይቀሩም። ወይስ 'የተፈሩ፥ የተከበሩ' ወይም 'ባለግርማ ሞገሱ' ይባሉ ይሆን? የቃሉ ትርጉም ያንን ያመለክታልና። አንድ መጋቢ በቅርብ በዶክትሬት ተመረቀና 'ዶክተር ፓስተር እገሌ' ብለው እንዲጠሩት ተናግሮ እንደ ነበር ሰማሁ። ይህ በቅርብ ያነበብኩትን አንድ መጣጥፍ አስታወሰኝ።

ይሔይስ አዕምሮ የጻፈው ነው። *መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ* ብሎ የሰየመውን መጣጥፍ ለመጻፍ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ሲጽፍ አንድ ዶክተር የጻፈው መጽሐፍ ሲመረቅ ደራሲው፥ ለምን ማዕረጉን 'ዶክተር / ፕሮፌሰር' ብሎ እንዳልጻፈ ሲጠየቅ፥ በምዕራቡ ዓለም ይህ ጊዜው ያለፈበት ዘዬና በስም ብቻ መጠራት የተወደደ መሆኑን፥ በአገራችን ግን ለመኮፈስና ከሌሎች የተለዩ መሆንን ለማመልከት እና ለጉራ መቸርቸሪያ እንደሚውል በመጥቀስ ትምህርት እንዲሆን ብሎ አለመጠቀሙን ነቅሶ እንዳወጣው መናገሩ ነው። አያይዞ እውነትም አንዳንዶች ፕሮፌሰር እና ዶክተር ተብዬዎቹ የዩኒቨርሲቲዎቻችን ሰዎች ምኝኛ የሚያሳፍሩ መሆናቸውን በዝርዝር ጽፎአል።

በኛዎቹ ፓስተር፥ ነቢይ፥ ሐዋርያ፥ ወዘተ፥ ዘንድም ተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል። ማዕረጉ ቅርበትን የሚያርቅ እየመሰለኝ ማዕረጓን ከስማቸው መጠሪያ ጋር ሳልጨምር በጥሬ ስማቸው እገሊዬ እያልኩ ስጠራቸው በግልጽ ባይነግሩኝም የሚያኮርፉ አገልጋዮች አጋጥመውኛል። ስልክ ሲደውሉም ገና ድምጻቸውን ሰምቼ በስም ሳልጠራቸው በፊት ፓስተርን ረገጥ አድርገው፥ 'ፓስተር እገሌ ነኝ' የሚሉኝ ጥቂት ወንድሞች አሉ። ባለቤታቸውና ልጆቻቸውም ሳይቀሩ እንደዚያ የሚጠሩአቸው መጋቢዎችም አሉ።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በከተማችን አቅራቢያ ያለች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ባዘጋጀችው ኮንፍራንስ ላይ የስብሰባ ጥሪ ወረቀት ተልኮልን ሳነብብ (እንደ ጸሐፊ የፊደል ግድፈቶችንም እያየሁ አነብብ ነበርና) በዚያ ወረቀት ላይ "ፖስተር እገሌ (ስም ተጽፎ) ስለሚያገለግሉን በቦታው ተኘተው እንዲካፈሉ እንጋብዛለን" የሚል ተጽፎአል። በሰፈር ጸሐፊ የተጻፈ መሆኑ ይታያል። 'ተገኝተው' ለማለት 'ተኝተው'፥ እና 'ፓስተር' ለማለት 'ፖስተር' ብለው ነበር የጻፉት። አላስተዋሉትምና የፊደል ግድፈት ሆነ እንጂ ነገሩ እውነት ነው፤ አንዳንድ ፓስተሮች ፖስተሮች ናቸው።

## ሥልጣንና ወንበር

ይህንን አሳብ ከላይ በአንድ ስፍራ አንስቼዋለሁ። ማዕረግና ሹመት ብቻ ሳይሆን ስለ መተዳደሪያ ደንቦች ስናጤን እንደተመለከትነው አንዳንድ መጋቢዎች ባለ ሙሉ ሥልጣን ሆነው መንፈሳዊውን ምግብ የመመገቡን ብቻ ሳይሆን አስተዳደሩንም ገንዘቡንም ጠቅልለው ከሚውጡት በላይ ጎርሰው አይውጡት አይተፉት ይሆንባቸዋል። መትፋት አይፈልጉም፤ ሊውጡ ሲሉ ደግሞ ይታነቃሉ። መጋቢ ሁሉ የአስተዳደር ወይም አገዛዝ ስጦታ አለው ማለት አይደለም። ከኖረው ደህና፤ ብቻውን ለምን ከፍ ዝቅ ይላል? ሙሴ ይህንን ሊያደርግ ሞክሮ እርሱም ሕዝቡም ሊያርሩ ትንሽ ሲቀራቸው ነው የዮቶር ምክር የደረሰለት፤ ዘጸ. 18። ይህኛውም ስጦታው ካለው ከሌሎቹ ጋር አብሮ ይተግብረው፤ ካልሆነ ግን፥ *እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።* (ሐዋ. 6፥4) እንዳሉት በዚህ ለመትጋት ሲል ራሱ አካልን በሙሉ ሊሆን ከሚሞክር ሌላውን ለሌሎቹ ብልቶች ቢተውና ቃሉን መመገቡን ቢተጋበት ያምርበታል።

## ንዋይና ገንዘብ

በ90ዎቹ መጀመሪያ የሴሚነሪ ተማሪ ሳለሁ በጀመርናት አንዲት ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያና የውስጥ አሠራር ደንብ መጋቢ በጊዜው ባይኖረንም እንኳ በሚኖርበት ጊዜ መጋቢው ከሽማግሌዎች ጋር እንደሚሠራና ገንዘብን ጭራሽ በትንሿ ጣቱም መንካት እንደሌለበትም በግልጽ አሰፈርን። ከዓመታት በኋላ ለመጋቢነት ከታጨት መካከል አንዱ መጥቶ ከጠየቃቸው ቀዳሚ ጥያቄዎች አንዱ የገንዘብ ወጪና ገቢዋን ደብተር ለማየት መፈለጉ ነበር። ይህ ሰው መጋቢ ሆኖ ተሾመ። ብዙም ሳይቆይ አንድ ቀን ከአንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌ ጋር፥ "እንደዚህ መተዳደሪያ ደንብ ለእግዚአብሔር ሥራ እንቅፋት የሆነ ነገር የለም" አሉ። ሁለቱም፥ መጋቢውም ጭምር፥ እዚያ አልቆዩም።

አሁን በማገለግልባት ቤተ ክርስቲያንም ደንባችን እንደዚያ ስለሆነ እኔ ስለ ገንዘብ የምሰማው በዓመት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ስናደርግ ከጉባኤው ጋር ነው። ይህ ለመጋቢ የእረኝነት አገልግሎት ጤናማ ፈር ነው ብዬ አምናለሁ። የሚያበራየው በሬ አፉን መታሰር እንደሌለበት አገልጋይም የሚያስፈልገው መደረግ አለበት። ይህ የታመነና በቃሉም በግልጽ የተጻፈ ነው። ይሁን እንጂ የመጋቢ ምድራዊ ኑሮ ሰማያዊውን ጥሪና ዋጋ የሚያስዘነጋ መሆን የለበትም።

## ምቾትና ድሎት

ወንጌላዊ ደሉ በሰበከው አንድ ስብከት ላይ ከፊት ወንበሮች ላይ የተኮለኮሉ መጋቢዎች ነበሩ። ከጉባኤው ታዳሚዎች ጋር ሲነጻጸሩ ሁሉም ያማሩና የለበሱ፥ የፈረጠሙና የወዙ፥ የወፈሩና ቦርጭም ያበቀሉ ናቸው። እንደዚህ መሆን በራሱ ክፋት ባይኖርበትም ንጽጽሩ ያፈጠጠና የሚያሳጣ ስለነበር እነዚህን ተመለከተና፥ "አሁን እናንተ መጋቢዎች ናችሁ ወይስ ተመጋቢዎች?" ብሎ ጠየቀ፤ ተገቢ ጥያቄ ነው።

አገልጋይ ሊያገለግል ተጋብዞ የሚስተናገድበት የክርስቲያን ቤት ካልጠፋ በቀር ሆቴል ባያድር የተመረጠ ነው። በቤተ ክርስቲያናችን በመስተንግዶ የተባረኩ ወገኖች በመኖራቸው ችግር የለብንም። በቅርብ የጋበዝነው አገልጋይ ግን የሆቴል ደረሰኝም ቀድሞ እንዲላክለት በመጠየቁ ስለተጋበዘ ብቻ ባይጥመንም አደረግን። በቤት መስተናገድ በረከት ነው፤ ለአገልጋዩ ለራሱም፥ ለሚያርፍበት ቤትም። ወጪው እንኳ ቢሰላ ለአገልጋዩ ቢለገስ ይሻል ነበር።

ከሁለት ዓመታት በፊት ያለሁበት አገር ኢትዮጵያውያን መጋቢዎች ዓመታዊ ስብሰባ ይደረግ ነበር (ለ9 ወይም 10 ቀናት ነው የተደረገው)።

እና ያረፉበትን ሆቴልና የቆይታውን ሁኔታ ስሰማ ደነገጥኩ። ለአንድ መጋቢ ለ10 ቀን ቆይታ የወጣው ወጪ ምንም ሳይጋነን አገር ቤት የሦስት አማካይ አገልጋዮች የዓመት ወጪ እንደሚያህል አሰላሁ። ይህን ያሰላሁት ራሴ እንደምቆይ ሆኜ ሆቴል ለመያዝ በመሞከርና የምግብ ወጪውንም በማስላት ነው። ደግሞም ተሳታፊ ከነበረ አንድ ወንድምም በማረጋገጥ ነው። እየሠራሁ ስላለሁት የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ሥራ መርዳት እንዲችሉ ጉዳዩን ለጉባኤው እንዲያቀርብ ከተሳታፊዎቹ መካከል ሌላ አንድ ወንድም በግል ጠየቀኝ። ቀደም ሲል ለሰሜን አሜሪካ አብያተ ክርስቲያናት (ለእነዚህም ጭምር) የጥያቄ ደብዳቤ በትኜ አንድም መልስ አላገኘሁም ነበርና ካቅማማሁ በኋላ ጊዜ ከሰጡት አሳቡን ሊያካፍላቸው እንደሚችል ፈቃዴ መሆኑን ነገርኩት። ዋናውን ፍሬ ነገር የያዘውን ሰነድና ናሙና ሥራዎቹን በአስቸኳይ እንድልክለት ነገረኝ። በአስቸኳይ ላክሁና በማግስቱ ሳይደርስ ሲቀር ደውሎልኝ ገና እንዳልደረሰና ለምን እንዳልደረሰ ጠየቀኝ። እኔም መላኬንና ስሙንና ሆቴሉን በትክክል መጻፌን ነገርኩት። "ይኼ'ኮ ስንት ፕሬዚደንቶችና መሪዎች የሚያርፉበት ሆቴል ነው። እንዴት እንደዚህ ያዘገያሉ?' ብሎ ተቆጣ። ያኔ ነው ስለ ሆቴሉ ትንሽ ምርምር ያደረኩት። እውነትም ያ ሆቴል ስሙ-ገናና እና በዚህ አገር ካሉ ትልልቅና ውድ ሆቴሎች መጀመሪያ መደዳ ካሉት አንዱ ነው። የምቾትና መዝናናት ፍላጎትና የእይታ መዛባት የተጣባቸው መጋቢዎቻችን ቁጥር ጥቂት አይደለም።

ደረጀ በመዝሙሩ፥ "ከንግዲህ የቀረኝ ሃያ ሰው ሰብስቤ፥ ኪሳቸው ኪሴ ነው ለወር ለቀለቤ" እንዳለው በቀን 12 እና 16 ሰዓት እየሠሩ ለጌታ ቤት ሥራ ከሚሰጡ ክርስቲያኖች የተባረኩ እጆች በሚወጣ መባእ መዝናናት የሚቃጣቸው በጣም በረከቱ። በዚሁ ሁኔታ በሚመጣ ገንዘብ አገር ቤት ቪላዎች ያሠሩና የሚያሠሩ መጋቢዎች መኖራቸው መቼውንም የሚያስተዛዝብ ነው። አንዲት የአገራችንን ባለ ሥልጣን ሚስት የባሏ ደሞዝ 4,500 ብር ብቻ መሆኑን ስትናገር ያየ አንድ ተቺ በአንድ ቴሌቪዥን ጣቢያ፥ "የሱ ያ ከሆነ የሷ ከሱ ማነስ አለበት። ሌላውን ትተን የያዘችውን የ$50,000 ዶላር የእጅ ቦርሳ ብቻ እንኳ ብናይ ውሸቷን መሆኑን እናውቃለን" አለ። ስለ መጋቢዎቻችን መዋዕለ ንዋይ አያያዛቸው ለመጠየቅ ሳይሆን እዚህ ቤት ቢገዙ ወይም ቢያሠሩ ጥያቄ ስለሚሆን ይሆን እዚህ አንድ መልክ እዚያ ሌላ ሥራ የሆነው?

## እከከኝ ልከክልህ

አንዳንድ መጋቢዎች ሌላውን የማይወቅሱበት፥ የማይገስጹበት ዘመን ላይ ደርሰናል። እንዲያውም እንዳጠፉም እያወቁ ሲያሞካሹት፥ ሲያሳብጡት፥ ስሞታ የሚያቀርቡ ምእመናንን ሲዘልፉና በጉባኤ ሲገስጹ መስማት እንግዳ መሆን አቁሞአል። በአንዲት ቤተ ክርስቲያን የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ምእመናን በመጋቢው አንዳንድ እርምጃዎች ቅሬታቸውን ቢገልጡም መጋቢው ሊሰማቸው አልፈለገም። ቅሬታቸውን ያቀረቡት ከቃሉ አንጻር ከመስመር የወጡ ጉዳዮች ላይ ነው። እንደ ቃሉ በጉዳዩ ለመምከር በቅርባቸው ያለ አንድ መጋቢ ጠርተው እንዲሸመግላቸው ጋበዙት። ይህኛው መጋቢ ሄዶ ጉዳዩን በመዳኘት ፈንታ ከመጋቢው ጎን በምቆም ስሞታ አቅራቢዎቹን በመደዳ ወነጀላቸው። ከዚያ ምንም ሳይሉ ወጡ፤ አልተመለሱም። ቁጥራቸው ጥቂት ስላልነበረ በአቅራቢያ ሌላ ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን መሥርተው እያመለኩ አሉ። የምእመናንን ስሞታ መናቅ የተጠናወታቸው ከወፈሩ ሰው አይፈሩዎች የበዙበት ዘመን ላይ ነን።

ይህንን የሚመስል ብዙ ምሳሌ መስጠት እችላለሁ። በዙሪያችን ከምናያቸው ይልቅ በቃሉ ያየነውን አንዱን ልናገር። ጳውሎስ ጴጥሮስን እያስመሰለ በግብዝነት ሲመላለስና ሰዎችን ለማስደሰት ሲታገል ሲያየው ፊት ለፊት ነበር የገሰጻውና የፈረደበት፤ *ነገር ግን ኬፋ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ ፊት ለፊት ተቃወምሁት፥ ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና፤* ገላ. 2፥11። ኬፋ ወይም ጴጥሮስ ያደረገውንና ጳውሎስ በግልጽ በሁሉ ፊት የገሰጻውን ተግሳጽ ከቁ. 12-14 እንዲህ ተጽፎአል፤ *አንዳንድ ከያዕቆብ ዘንድ ሳይመጡ ከአሕዛብ ጋር አብሮ ይበላ ነበርና፤ በመጡ ጊዜ ግን ከተገረዙት ወገን ያሉትን ፈርቶ ያፈገፍግ ነበርና ከእነርሱ ተለየ። የቀሩትም አይሁድ ደግሞ፥ በርናባስ ስንኳ በግብዝነታቸው እስከ ተሳበ ድረስ፥ ከእርሱ ጋር አብረው ግብዞች ሆኑ። ነገር ግን እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄዱ ባየሁ ጊዜ በሁሉ ፊት ኬፋን። አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር፥ አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልሃቸው? አልሁት።* ተቃወመና ፈረደበት፤ ያውም በሁሉ ፊት። ጴጥሮስ ይህን ያደረገው ባለማወቅ ወይም በትምህርት ጉድለት አይደለም። ጴጥሮስ በጸጋ ስለ መዳን እና ከሕግ እስራት አርነት ስለመውጣት አሳምሮ ያውቃል። ስለዚህ ጳውሎስም የቡድኔ ተጫዋች ነው ብሎ ጀርባውን መታ መታ አድርጎ አላለፈውም።

## ፳፥ <u>መደምደሚያ</u>

ስለ መልካም መጋቢዎቻችን እግዚአብሔር ይመስገን። እነርሱም ይባረኩ። እነዚህ ወገኖች ከጸሎታችን አይጥፉ።

በጠቅላላው መጋቢዎች፥ አሁን ያሉትም የሚመጡትም በውስጣቸው ያለውን ከጌታቸው መቀበላቸውን ማረጋገጥ ቢችሉ ጥሩ ይሆናል። እረኝነትን ከመልካሙ እረኛ ቢቀስሙና ሙያ ባያደርጉት ውብ ነው። መጋቢዎች ከገንዘብ አስተዳደርና ከመዝገብ አያያዝ የወጡ ይሁኑ። ይህች ብዙዎች 'መጋቢዎችን' የምታስቆጣ ብትሆንም ለአገልግሎት ጤንነታቸውና ለእምነታቸው ተገቢው አካሄድ ነው።

እንዲያውም አንዳንድ መጋቢዎች ቢቀመጡና ተራቸውን በጉባኤያቸው ቢገለገሉ እንዴት መልካም ነበር! በጉባኤያቸው የሚያገለግል ከጠፋ ባለመመገባቸው ምክንያት ተጠያቂዎቹ ራሳቸው ናቸው። ምእመናን ደግሞ ጸጋቸውን ቢረዱና መጋቢ ባይኖርም ትኩስ ቃል እየበሉ መኖር እንደሚቻልም ማወቅ ቢችሉ ጥበብ ነው። የስደቱ ዘመናት ለቤተ ክርስቲያን ያስተማረው ትልቅ ነጥብ ይህ ሆኖ በነጻነት ማግሥት እንደሞተ ያህል ከልብ የተረሳ እውነት ነው።

አብያተ ክርስቲያናት፥ በግልጽ የተጻፈና የተቀመጠ መተዳደሪያ ደንብና የአሠራር መመሪያ ይኑራችሁ። በውስጡ ደግሞ የመጋቢ የአገልግሎትና የኃላፊነት መደብ በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ ይቀመጥ። ብዙዎች የምዕራቡ ዓለም የአበሻ አብያተ ክርስቲያናት ይህ የላቸውም፤ ወይም ሆን ተብሎ እንዳይኖራቸው መደረጉ ይስተዋላል። ይህ ትልቅ ስሕተት ነው። ቤተ ክርስቲያን ሕያው ዘአካልም ድርጅትም መሆኗ አይጥፋን።

እግዚአብሔር ከአርያም ይባርካችሁ። አሜን።

*ዘላለም መንግሥቱ © 2013 (፪ሺ፮፮) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት*

# የተመችቶኛልና የአልተመቸኝም አንቀጾቼ

©ሰሎሞን ጥላሁን

## ሀ. የአልተመቸኝም አንቀጾቼ :-

1. እኔ አልተመቸኝም! ከመጀመሪያው ጥሪአችን ጋር የተፋታ፣ የቁሳዊው ዓለም ስኬት ቀመር የሚፈበረክበት፣ የክርስቶስ ወንጌል የይስሙላ የሚነገርበት **ምስባክ አልተመቸኝም!**

2. መስቀል ተሸክሞ ራስን ክዶ እለት እለት ክርስቶስን የመከተልን ጥሪ ሽሮ በምትኩ አንድ ወገናዊና ሁልጊዜ ትባረካላችሁ ብቻ የሆነ የምድራዊ ተስፋ እየተናገሩ ስለ ክርስቶስ የሚከፈልን ዋጋ እንደውርደት የሚቆጥርን ድምጽ **መስማት አልተመቸኝም!**

3. የክርስቶስን ስም ችግር ለማባረሪያ፣ ሰይጣንን ለመቆጣት እንደድጋም እየፎከሩ በሕይወት ጌትነቱን በቋሚነት እየካዱ በሚኖሩ ሰዎች መካከል **መገኘት አልተመቸኝም!**

4. ክርስቶስን በገዛ ቤቱ ጥግ አስይዛ በገበያው ሕግ በነጋዴዎቹ አስተሳስብ የምትመራ “ቤተ ክርስቲያን” **ማየት አልተመቸኝም!**

5. የተቀቡ የእግዚአብሔር “አገልጋዮች” መሆናቸውን እየተናገሩና እያስነገሩ በመጣጫዊ አሰራራቸው በተግደርዳሪ ከሚኖረው ሕዝብ ባገኙት ገንዝብ ራሳቸውን የሚያደልቡትን ነጋዴዎች **እያዩ መኖር አልተመቸኝም!**

6. የታላቁ ተልእኮ አደራ የሆነውን ደቀ መዝሙርን የማፍራት ቀዳሚ ሥራ ጨርሶ የተወችና ቃሉን “ሀ” ብለውም ሆነ “ዋ” ብለው ባልተማሩ የመድረክ ላይ ቧልተኞችና ቀልደኞች የለወጠች ቤተ ክርስቲያን **ማየት ጨርሶውኑ አልተመቸኝም!**

7. በቀዳሚ ጥሪ ልባቸው ተነክቶ በልብ ለውጥ ተሰብስበወባት የነበረች አሁን ግን የአገዛዝ መስፍናዊነት፣ የአስተምህሮዝብርቆሽ የእግዜርን ትሩፋን ግራ አጋብቷቸቸው የሚበረግጉባት፣ ወይ ጥግ የሚይዙባት ቤተ ክርስቲያን ተብላ የምትጠራ ከመንግሥት ሕግ በቀር የሰማዩ ሕግ የማያውቃት ማሕበር **ማየት እንዲያው ፈጽሞ ሊመቸኝ አልቻለም!**

8. ለክርስቶስ ወንጌል ባእድ የሆኑ ትምህርቶችን፣ ሐሰተኛ ትንቢቶችን፣ መባ -የፍቅር ስጦታ - የአገልግሎት ድጋፍ ገንዘብ ምዝበራዎችንና ልዩ ልዩ ማታለሎችን ሃይ የማትል፣ የተግሣጽ አቅም የሌላትና ይልቁንም በተግባሯ አበጃችሁ እያለች የምትገኝ **ስመ ቤተ ክርስቲያን በቃ አልተመቸችኝም!**

9. እግዚአብሔር ለልዩ ልዩ አገልግሎት በአማኞች ውስጥ ያመቀውን ልዩ ልዩ ጸጋና ስጦታዎች አፍና ይልቁን ከእነርሱ በምትሰበስበው **ገንዘብ የምትታመን ቤተ ክርስቲያን በጭራሽ አልተመቸችኝም!**

10. “እንዲህ መሆኑን ባውቅ ኖሮ ባልመጣሁ ይሻለኝ ነበር” የሚሉባት፣ እውነትን አግኝተው እውነት የጠፋባቸው ያሉባት፣ አገልጋዮቿ የሚማረሩባት፣ የሚሞቱላት የሚሻሩባት ገዳዮቿ የሚሾሙባት፣ **ግራ የምታጋባ ስመ ቤተ ክርስቲያን ጨርሶውኑ አልተመቸኝም!**

11. ልጆቿ ወደላይ አባታችን ሆይ እያሉ እየጸለዩ ወደጎን ወንድምና እህትማማችነትን የሚካካዱባት፣ እንኳን የሰማይ ቤተሰብ ጠንካራ የአገር ማሕበር መሆን ያቃታትን **ስብስብን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ማለት ተናነቀኝ አልመችህ አለኝ!**

12. ልምዳቸውን፣ ክብራቸውን፣ ቁሳቁሳቸውን፣ ሥልጣናቸውን፣ በ “አገልግሎት” የዞሩባቸውን አገሮች፣ እንትን ምናምን ቅብጥርጥር አንድም ቃለ እግዚአብሔር የሌለበት ዝብርቆሽና እንሰብከዋልን ብለው ያነበቡልንን ጥቅስ ያብራሩልናል ብለን ስንጠብቅ ከጥቅስ ወደ ጥቅስ በአሰልቺ ዙረት መኖራችንን ለማረጋገጥ አሜን እያሰኙ **መቀመጫዬ ላይ ሆኜ የሚያንከራትቱኝን ሰባኪያንና መምህራን ማለት ተናነቀኝ አልተመቸኝም!**

13. የወንጌል ጤንነት ሲበረዝ እያያዩ ቢያውቁትም ምንም ያልመሰላቸውና በዚህ ጉዳይ ቢናገሩ ከሚመጣው ቅይማት መከባበርን የመረጡ አሳልፎ ሰጪ ዲፕሎማቶችን **እንደ ወንጌል ባላደራ ልጠራቸው አልተመቸኝም!**

14. ለአካባቢ ጥበቃና ስነ ምሕዳር፣ ለሰው ልጆች ሰላምና ፍትሕ ትንቢታዊ ድምጽ የማታሰማ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ የጨውና የብርሃን ሕልውናዋ የማይታወቅ ለደሃው ግድ የሌላት የገንዘብና የጉልበት ወጪዎቿ ወደ ውስጧ ብቻ የሆነ ራሷን ወዳድና **ጥሪዋን የዘነጋች ቤተ ክርስቲያን አልመችህ ብላኛለች!**

15. እናም ራሴም አልተመቸኝም በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶችና “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅለሃል አሁን ሕያው ሆነህ አትኖርም ክርስቶስ በአንተ ይኖራል፣ በሥጋ የምትኖረው ኑሮም በወደደህና ስለአንተ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት ነው” እያልኩ ብነግረውም **በቀን 24 ጊዜ ከመስቀል እየወረደ አበሳ የሚያሳየኝም “እኔ” አልተመቸኝም!**

16. የተመቸኝ የተሐድሶ ጥማት ነው፣ የለውጥ ረሃብ፣ ጉድፍ የሌለው ንጹሕ የአምልኮ ማእጠንት፣ የክርስቶስ ምስፍና የሕይወት ንጽሕና ፣ ያለባት የካህናት ሕዝብ የሆነች ማሕበር የማየት ህልም ተመችቶኛል!

17. እናንተስ ምንድን ነው ያልተመቻችሁ? ምንስ ተመቻችሁ?

## ለ. የተመችቶኛል አንቀጾቼ :-

1. ሊገለጥ ከሚቻለው በላይ ሰማያዊ ውበት ያላት - ጥሪዋ ያማረ ድምጿ ሰላማዊ፣ ምስረታዋ ከሰማይ መገኛዋ በምድር፣ ታሪኳ የዘመናት አባላቷ ብዙ ሕልውናዋ በሚጠሏት መካከል

የግዢዋ ዋጋ የአምላክ ልጅ ደም የሆነ ዓለም ሳይፈጠር አባልነቴ የተረጋገጥባት **የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ስላለች እጅጉን ተመችቶኛል!**

2. እንደሰማይ ከዋክብት በምድር የተረጨች፣ ከቋንቋ ከነገድ ከኑሮ ደረጃ፣ ከቀለም ከጾታ የተቀናበረች በልዩነት፣ በልዩታም (ዩኒክነስ) ሆነ በልዩ ልዩነት ብዛት የሚመስላት የሌለ፣ ዓይነተ ብዙ ሆና አንድ ጌታ ያላት፣ አንዴ ወይን ሲላት አንዳንዴ እርሻዬ ሌላም ጊዜ ሙሽራ ናት፣ ደግሞም የጌታዋ አካል በይ ሲላት የእግዜር መንጋ ናት ሲሻትም ቤተ መቅደሱ ወይም የእግዚአብሔር ቤተሰብ ናት አንድ ሆና **ስመ ብዙ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ስላለች ጮቤ እየረገጥኩ ተመችቶኛል!**

3. የትንሣኤው ኃይል መገለጫ የሞት ኃይላት ድምጽ መደምሰሻ የተስፋ አዋጅ ማዕከል የደፋሮች መናኸሪያ የገሃነም ደጆች የማይችሏት **ለክፉ ኃይላት መቅሰፍት የሆነች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ስላለች ፈጽሞውኑ ተመችቶኛል!**

4. የእግዜር ልዩ ልዩ ጥበብ መታያ ለሰማይ ኃይላትና ሥልጣናት ትንግርትና ምሥጢር የሆነች ለምድር ነገሥታት ችግር ቢያጠፏት አትጠፉ ቢገድሏት አትሞት ይህች **የሰማይ ሥራ በምድር ስላለች እፎይ ደስ ብሎኛል ጨርሶውኑ ተመችቶኛል!**

5. እኔ ቢመቸኝ ባይመቸኝ ምርጥ ዘርና አረማሞ፣ ቡቃያና እሾህ ተቃቅፈው እንዲበቅሉባት አውቆ ባለቤቱ አጨዳ የከለከለባት ጊዜ ለራሱ የቀጠረባት እርሻ መሆኗን አውቄ **ለራሴ ተጠንቅቄ የምኖርባት ቤተ ክርስቲያን ስላለች አሜን ብዬ ተመችቶኛል!**

6. ምን ይሄ ብቻ በመስቀል ጣር ሞት በዋጋ የገዛቸው፣ በመንፈሱ የሙላት ልክ በጸጋው ሥጦታ የባረካቸው፣ ነፍሳትን ማራኪ የቁርጥ መልእክት ተልኳውያን ቤተ ክርስቲያን ተካይ ወንጌላውያን፣ ደግሞም የቃሉ ተንታኝ የአስተማሪው አንደበት ያላቸው **ትጉህ ቅቡአን ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ስላለች እሰይ ተመችቶኛል!**

7. ለእውነትና ለጽድቅ የተወጉ፣ ለመከተላቸው ምልክት የያዙ፣ ጌታቸው በሄደበት የሄዱ፣ የመሪአቸውን ፈለግ የተከተሉ፣ ሚዛን ከላይ ሲመጣ ችንካራቸውን የሚያሳዩ፣ ከኃጢአት ጋራ ታግለው በተስፋ ተደስተው በእምነት ጸንተው የሚጓዙ ራሳቸውን ክደው መስቀሉን ተሸክመው እለት እለት የሚከተሉ ያሉባት **ማሕበረ ደቀ መዛሙርት ስላለች ተመስገን ተመችቶኛል!**

8. ከመብል የትኛውን ልብላ፣ ከልብስ የትኛውን ልልበስ፣ ከመኪና የትኛውን ልንዳ፣ ከቤት የትኛው ውስጥ ልኑር ከሚል "የብልጽግና ሥቃይ" ተርፈው የዚህን ምድር እንጡራ በማካፈል በሰማይ መዝገብ የሚያከማቹ ፣ ምን ልብላ፣ ምን ልልበስ፣ ምን ልጫማ፣ የት ልኑር ለሚሉ ጎስቋሎች የሚቆረሱ ባስደናቂ የቸርነት ስጦታቸው የሚያስቀኑ ለደሃ እየሰጡ ለእግዜር አበዳሪዎች የሞሉባት **የደጉ አምላክ ደግ ልጆች የታጎሩባት ቤተ ክርስቲያን ስላለች እፎይ ብዬ ተመችቶኛል!**

9. የፈጣሪን መኖር አምላክነቱን፣ የፍጥረት ሕግ ደንጋጊና የሚታይ የማይታየው ነገር ባለቤትነቱን፣ ሲያሻቸው በፍልስፍና ደርዝ፣ አለያም በከርሰ ምድር ምርምር፣ ወይ በሰላ ምላስ የእምነት ክርክር፣ ደግሞም ክርስቶስ ትሥጉቱ - በመለኮቱ፣ ሞቶ ለመንሣቱ ለድንቅና ለታምራቱ፣ ለቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ መለኮትነት፣ ለምግባር ሰጭነትና በላጭነቱ የሚሟገቱ **የእምነት አቃቢያን (አፖሎጂስት) ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ስላለች ኮራ ያለ ምቾት ተመችቶኛል!**

10. በብርሃንና በጨው አገልግሎቷ የምትታወቅ፣ የሰላምና የፍትሕ ተሟጋች፣ የማሕበራዊ ተልእኮዋን ስለክርስቶስ ስትል የምትፈጽም፣ ሕልውናዋ በድሆችና በተጨቆኑት መካከል የሆነ **ነብዩት ቤተ ክርስቲያን በሕይወት ስላለች ተመችቶኛል!**

11. የኅብረትን እንጀራ የሚቆርሱ የጌታቸውን ራት ገብቷቸውና ተገብቷቸው የሚቋደሱ፣ በጋራ ጸሎት የሚተጉ፣ ቅዱሱ መንፈስ በልባቸው የሚፈስ በሰራዊት ጌታ ፊት እውነተኛ አምልኮን በደስታ፣ በአድንቆት፣ በትህትናና በፍርሀት የሚያቀርቡ ያሉባት፣ የማይጠፋ የአምልኮ እሳት ባለ ንጹሕ ማእጠንት የምታቀርብ **በእውነተኛ አምልኮ የምታገለግል ቤተ ክርስቲያን ሰላለች ተመችቶኛል!**

12. ከዓለም ፍልስፍና ያልተጋባች፣ እንደ ድርጅት ብርቱ የአመራር ስልት ያላት፣ ዘመኑን በዋጀ የአገልግሎት ፍልስፍና፣ በጸጋና በአገልግሎት ስጦታዎች አባላትን አደራጅታ በክርስቲያናዊ ትምህርት ሕያዊት አካል ለመሆን የምትገነባ፣ ክርስቶስ ራስ ሆኖ ሕዝቡ አገልጋይ የንጉሥ ካሕናት የሆነባት **የአዲስ ኪዳን መሲሐዊት ቤተ ክርስቲያን በምድር ተበትና በመኖሯ ተመችቶኛል!**

13. የእርስ በርስ ጥላቻ ወይም ከራስ ወዳድነት ጉልበት የሚመነጨው "ወግዳዊነት" (ኤክስክሉዥኒዝም) የማይታይባት ከጉዳቷ የምትማር የሰዎች ጉባኤ በመሆኗ ግጭት ቢገጥማትም የሰላምን ወንጌል በልኳ ተጫምታ እርስ በርሷ ታርቃ የምታስታርቅ ለእግዜር እጅ ሥራ ለፍጥረታት ሁሉ ፍትሕ ግድ የሚላት ምሉእ ትምህርተ መለኮት የምታራምድ በአስተዳደር፣ በአስተምህሮቷና በምግባሯ ልእቀት **ርትእት የሆነች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በምድር ገጽ ስላለች ተመችቶኛል።**

14. እነዚህን የምቾት አንቀጾቼን በአንዷት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተከማችተው ባላገኛቸውም ብዙዎቹ በልዩ ልዩ እውነተኛ የወንጌል ማሕበራት ወስጥ ሰለሚገኙ የትሩፋኑም ተስፋ **የተሐድሶም እምቅ ኃይላት የማራናታ ማማዬ ናቸውና ተመቸቶኛል!**

15. እናንተስ ምንድን ነው የተመቻችሁ? ምንስ አልተመቻችሁም?



© ሰሎሞን ጥላሁን solmzz@yahoo.com

# ሰላም . . . ቻዎ

ሰላም ለዲፕሎማቶች
የወንጌል ባለ አደራ አገልጋዮች
ሰባኪ አስተማሮች
ፓስተር ሽማግሎች
ደግሞም ባለ ብዙ ማእረጎች፤

የወንጌል ጤንነት ሲበረዝ እያያችሁ
ምንም ያልመሰላችሁ
ከቅይማት መከባበርን መርጣችሁ
እግዜርን ያሳዘናችሁ፤
ሰላም ዲፕሎማቶች እንዴት ናችሁ?

ደግሞም እንዴት ናችሁ አንበሶቼ
የመድረክ ላይ ነብሮቼ
መልክት አልባ ኮሜዲያን ኮሚኮቼ
የሐሰት ነቢያት አራዶቼ፤
ቻዎ ፀሐይ እስኪወጣ።

ሰሎሞን ጥላሁን

---

# ለካስ

ለካስ ይናፍቃል?
ከቶ ያላዩት ውበት ከቶም ያልሰሙት ቃል
ወዘና አጠውልጎ . . . ደምግባት አርቆ
ማስተዋልን ሰልቦ . . . ኀሊናንም ሰርቆ
ልብን እያደማ አእምሮን ይፍቃል?
ከቶውን ያላዩት
የማያውቁት አገር ለካስ ይናፍቃል?
. . . ለካስ . . . ።

ዘ. መ. ለጤጅ አሳላፊው ነህምያ
January 2011

# እስላም እና ክርስትና (ንጽጽራዊ አቀራረብ)




*የመጽሐፍ ሒስና ግምገማ*

*ደራሲ፥ ዶ/ር ሙሓመድ ዓሊ አልኹሊ*

*ተርጓሚ፥ አይታወቅም*

*አሳታሚ፥ ሑዳ ፕሬስ ሊሚትድ፥ አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ*

*የገጽ ብዛት፥ 91*

*የኅትመት ዘመን፥ 1989*

## ክፍል 3

ባለፉት ሁለት ክፍሎች በዶ/ር ዓሊ አልኹሊ የተጻፈውን እስላምና ክርስትና (ንጽጽራዊ አቀራረብ) የተሰኘ መጽሐፍ በማሔስ ጸሐፊው መጽሐፍ ቅዱስን ስሕተት ሊያሰኝ የጣረበትን ነጥቦች ማየት ጀምረን ነበር። ያንን በመቀጠል በዚህ ክፍል ሌሎች የጸሐፊውን ነጥቦች ማየት እንቀጥላለን።

### ትክክለኛነት?

'ትክክለኛነት' በሚል ንዑስ ርዕስ ስር ኢየሱስ የተናገረው በአራማይስጥ ቋንቋ ሲሆን በዚያ ቋንቋ የተጻፈ ወንጌል አለመኖሩና በአንጻሩ ደግሞ የሙሐመድ ቋንቋ ዐረብኛ ሆኖ የተናገረው በቋንቋው መገኘቱን ይዘግባል።

**እዚህ ላይ ሁለት ሰዎች ከፊታችን አሉ። በአንድ በኩል በአራማይክ (የሶሪያ ቋንቋ) ተናጋሪ የነበሩና ስለሳቸው አንድም ነገር በአራማይክ ያልተዘገበ ኢየሱስ ሲሆኑ፤ እሳቸውን አስመልክቶ ዛሬ በእጃችን ያለው መረጃ የጠፉ ኦሪጂናሎች የትርጉም ቅጂ ብቻ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዐረብኛ ተናጋሪ የነበሩና ስለሳቸው የቀረቡ ዘገባዎች በሙሉ ነቢዩ ይናገሩ በነበረው ዐረብኛ ቋንቋቸው ተጠናቅረው የምናገኛቸው ሙሐመድ ናቸው።**

እንግዲህ ጸሐፊው እንደ ንዑስ ርዕሱ ቃል 'ትክክለኛ' ሊል የፈለገው ኢየሱስ የተናገራቸው ነገሮች በአራማይስጥ ያለመጻፋቸውንና የሙሐመድ ደግሞ በዐረብኛ ተጽፈው መገኘታቸውን ነው። ጸሐፊው ቋንቋን ብቻ እንጂ ዘመኑን የዘነጋ ይመስላል። በአራማይስጥ የተጻፈ ወንጌል ኖሮ ኦሪጂናሉ ጠፍቶአል ካለ ጸሐፊው እየቃዠ ነው። አራማይስጥ የንግግር ቋንቋ መሆኑና ኢየሱስም ሆነ ደቀ መዛሙርቱ ይናገሩ የነበሩት በአራማይስጥ መሆኑ እውነት ነው።

አራማይስጥ ወይም ሱርስጥ ከዚያን ዘመን አራት መቶ ዓመታት በፊት በነበሩት ጊዜያት የአሶርንና የባቢሎንን ወረራ ተከትሎ የተስፋፋ ዋና ቋንቋ ነበረ። ከዚያ የትልቁ እስክንድርን ወረራ ተከትሎ ዋናው ቋንቋ ግሪክ ወይም ጽርዕ ሆነ። የሮም መንግሥት ሲገዛም እንኳ ሮማይስጥ የመንግሥት ሥራዎች ቋንቋ ሆነ እንጂ የስነ ጽሑፍንና የፍልስፍናን ቋንቋ ሊተካው አልቻለም። ይህ የሆነው የላቀ ቋንቋ ስለሆነ ነው። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትም በግሪክ ቋንቋ መጻፋቸው ትክክልና ተገቢ እንጂ ስሕተት የለበትም። አራማይስጥ በዘመኑ የጽሑፍ ቋንቋ አልነበረም። ዕብራይስጥም ራሱ እንኳ በዚያን ዘመን ክልላዊና ሃይማኖታዊ የጽሑፍ ቋንቋ ነበር እንጂ ብሔራዊነት ያለው የጽሁፍ ቋንቋ አልነበረም። አይሁድም ራሳቸው በንግግርና በመግባቢያነት የዕብራይስጥ ሳይሆን የአራማይስጥ ተናጋሪዎች ነበሩ። ዕብራይስጥን የሚያነብቡና የሚናገሩ እንደ ፈሪሳውያን ያሉቱ ቀናተኛ ሃይማኖተኞች ብቻ ነበሩ።

አዲስ ኪዳን በአራማይስጥ ሳይሆን በግሪክ የተጻፈ መሆኑ ከብዙ አንጻር ጠቃሚ ነው። አንደኛ፥ የዘመኑ ዋና መግባቢያ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለቀጣዮቹ 200 ያህል ዓመታት በአገልግሎት የቆየ መሆኑ ለክርስትና መስፋፋት ጠቃሚ አስተዋጽዖ አድርጎአል። ሁለተኛ፥ የግሪክ ቋንቋ ያደገና የበሰለ ብቻ ሳይሆን የደረጀ ቋንቋ መሆኑ ለጠንካራ ክርስቲያናዊ ስነ መለኮት ጅማሬና ዕድገት አስተዋጽዖ አበርክቶአል። ሦስተኛ፥ ለቤተ ክርስቲያንም አንድነት ተገቢ ድርሻ ኖሮታል። የአዲስ ኪዳን ቋንቋ ዕብራይስጥ ቢሆን ኖሮ የአይሁድ ተጋቦት አሕዛብን ሁለተኛ ዜጋ ባደረጋቸውም ነበር።

ከሁሉም በላይ ደግሞ ዋናው ነገር የአዲሱ ኪዳን ቋንቋ ሳይሆን መልእክቱ ነው። ወንጌሉን በአማርኛ ሰማን በቻይንኛ፥ በዐረብኛ ሰማን በፈረንሳይኛ ቋንቋው ሳይሆን የተላለፈው እውነት ነው ቁም ነገሩ። የእግዚአብሔር ቃል በአንድ ቋንቋ ተበይዶ የተቆለፈ ቃል አይደለም። ዋናዎቹን የዕብራይስጥ፥ የአራማይስጥ (ጥቂት የብሉይ ኪዳን ክፍሎች በአራማይስጥ ተጽፈዋል) እና የግሪክ ቋንቋ አውቀን በነዚህ ቋንቋዎች ብናነብብ ወይም በዘመናዊ ቋንቋ የተተረጎመልንን ብናነብብ መልእክቱ ሳይዛነፍ እናገኘዋለን። በመጀመሪያዎቹ ቋንቋዎች ማንበብ በጣም መልካም ቢሆንም እነዚያን አለማወቅ ደግሞ ጎዶሎነት አይደለም። ስለዚህ የኢየሱስ ቋንቋ አራማይስጥ ሆኖ በአራማይስጥ ወንጌል አለመገኘቱ ሊያስደንቅ አይገባም። ቀድሞ ኖሮ ግን አልጠፋም። ይህ ቅዠት ብቻ ሳይሆን ውሉን የሳተ ቅዠት ነው።

## ተቃርኖዎች?

ቀጥሎ ‘ተቃርኖዎች’ በሚል ርዕስ ስር ዶ/ር ዓሊ እንዲህ ይላል፥

> **ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ብትላቸውም፣ አራቱ የሐዲስ ኪዳን ወንጌሎች በተመሳሳይ ሁነቶች ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ ልዩነቶች ያሳያሉ።**
>
> **በእስላም ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ቁርአን ግን አንዳች ውስጣዊ አለመጣጣምም ሆነ ተቃርኖ የለበትም።**
>
> **እንደ የእግዚአብሔር የጠራ ቃል የትኛውን ነው የሚቀበሉት? ከአራቱ ተጻራሪ ወንጌሎች ጋር ሐዲስ ኪዳንን ወይስ ከማይናጋ ቋሚ ወጥነቱና የተሟላ ፍጹማዊ መጣጣሙ ጋር ቁርአንን?**

መቼም ምሳሌ አድርጎ በአንድም ስፍራ ተጨባጭ ነገር የማያቀርብ መሆኑ ባለፈው ክፍል እንደተመለከትነው አውቆ ለማወናበድ ወይም በጭፍን ለማምታታት ነው። እንጂ በወንጌላት ውስጥ እርሱ እንዳለው በመቶዎች የሚቆጠሩ ልዩነቶች አለመኖራቸውን ዶክተሩም ሳያውቀው አይቀርም።

ያነሣቸውን ሁለት ነጥቦች ግን እንመልከት። አንዱ የወንጌላት ተቃርኖ ያለው ሲሆን ሁለተኛው የቁርኣን ተቃርኖ የሌለበት መሆን ናቸው። በመጀመሪያ የወንጌላትን “ተቃርኖ” እንይ። ወንጌላት፥ አራቱ ወንጌላት በአራት የተለያዩ ጸሐፊዎች የተጻፉ የጌታ ትምህርቶችና ታሪኮች ናቸው። አንዳንዶቹ ታሪኮች በአንዱ ወንጌል ብቻ ሲገኙ አንዳንዶቹ ደግሞ በአራቱም ይገኛሉ። የእግዚአብሔር ቃል እንዲጻፍ ዋናውን ሥራ የሠራው መንፍስ ቅዱስ መሆኑን እናስተውል። ቅዱሳን ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው ተናገሩት፤ 2ጴጥ. 1፥21። ይህ ሳይዘነጋ ታሪክ እንደ ተራኪውና እንደ ተመልካቹ መሆኑንም እናጢን። ጸሀፊው ከሚመለከትበት አንጻር የተጻፈ ነውና። አራት ምስክሮች ስለ አንድ ክስተት ሲናገሩ ቃል በቃልና ሐረግ በሐረግ ተመሳሳይ መሆን አለባቸው ብለን መጠበቅ የለብንም። ታሪኩና የታሪኩ ይዘት ግን አንድ መሆን ይጠበቅበታል። የዓይን ምስክሮች እዳኛ ፊት ቀርበው የሚናግሩት ቃል በቃልና ሐርግ በሐረግ አንድ መሆን አለበት ማለት ተላላንት ነው። ልክ እንደዚሁ አንዱ ወንጌል ውስጥ የተጻፈው ሌላው ውስጥ ስላልተጻፈ ያንን ልዩነት ብለን አንወስድም። ሁሉም ወይም ከፊሉ ጽፈውት ቢቃረን ግን ሊሰኝ ይችላል።

ለምሳሌ፥ ጌታ በሁለት ዓሣና በአምስት እንጀራ ብዙዎችን የመገበበት ታሪክ በአራቱም ወንጌላት ተጽፎአል፤ ማቴ. 14፤ ማር. 6፤ ሉቃ. 9፤ ዮሐ 6። አንዱ በሁለት ዓሣ ያለውን ሌላው በአሥራ ሁለት ዓሳ ካለ ተቃርኖአልና ይህንን ተቃርኖዎች ቢል እውነትነት ይኖረዋል። የመስቀሉ ስቃይ ሞቱና ትንሣኤውም በአራቱም ወንገላውያን ተዘግቦአል። አገላለጻቸው ፍጹም አንድ አይደለም። ልዩነት ግን የላቸውም። ቁርኣኑ ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከአራቱ አንዱ የጻፈውን እንኳ አይቀበልም። አራቱም ግን አንድ ነው ቃላቸው። አራቱም ወንጌላት አንዱ የሌላው ቅጅ እስኪመስል ወይም በፎቶ ኮፒ እንደተባዙ ተመሳሳይ ቢሆኑ አራት ወንጌላት ባልኖሩና ባላስፈለጉም ነበር።

ሁለተኛው የቁርኣን ተቃርኖና ግጭት የሌለበት መሆን ነው። እውን በቁርኣን ውስጥ ግጭትና ተቃርኖ የለም? ሁሉን ለማቅረብ መጽሐፍ ይወጣዋል፤ እንደ ዶ/ር ዓሊ ቁርኣን ተቃርኖና ግጭት አለበት ብቻ ብሎ ምሳሌ ሳይሰጥ ላለመተው ጥቂት እነሆ፤

### ሀ) ፍጥረት በስንት ቀን ተፈጠረ? በ6? በ7? በ8?

> **ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረ፥ በዐርሹም ላይ ራሱን ያደላደለ (አምላክ)ነው። ነገሮችን (ሁሉ) ያስተናብራል፥ ይመራል። ከርሱ ፈቃድ በኋላ ካልሆነ በቀር (የሚያማልድ) አንድም አማላጅ የለም። ጌታችሁ አላህ ይህ ነው። ስለሆነም (በብቸኝነት) አምልኩት። አትገለፁምን?** 10፥3 (በተጨማሪ 7፥54፤ 10፥3፤ 11፥7፤ እና 25፥59 ተመሳሳይ አሳብ አላቸው።)

ይህ በ6 ቀን መፈጠሩን ይጠቅሳል። በ41፥9-12 ያሉት ቀናት ድምር ደግሞ 8 ይሆናል።

> **9፥ በላቸው፦ እናንተ በዚያ ምድርን <u>በሁለት</u> ቀኖች ውስጥ በፈጠረው አምላክ በእርግጥ ትክዳላችሁን? ለርሱም ባላንጣዎችን ታደርጋላችሁን? ያ (ይህንን የሠራው) የዓለማት ጌታ ነው።**
>
> **10፥ በርሷም ከበላይዋ የረጉ ጋራዎችን አደረገ፤ በርሷም በረከትን አደረገ፤ በውስጧም ምግቦችዋን (ካለፉት ሁለት ቀኖች ጋር) <u>በአራት</u> ቀናት ውስጥ፣ ለጠያቂዎች ትክክል ሲሆኑ ወሰነ።**
>
> **11፥ ከዚያም ወደ ሰማይ እርሷ ጭስ ሆና ሳለች አሰበ፤ ለርሷም ለምድርም ወዳችሁም ሆነ ወይም ጠልታችሁ፣ ኑ፤ አላቸው። ታዛዦች ሆነን መጣን አሉ።**
>
> **12፥ <u>በሁለት</u> ቀኖችም ውስጥ ሰባት ሰማያት አደርጋቸው፤ በሰማያቱም ሁሉ ነገሯን አዘጋጀ፤ ቅርቢቱንም ሰማይ በመብራቶች አጌጥን፤ (ከሰይጣናት) መጠበቅንም ጠበቅናት፤ ይህ የአሸናፊው፣ የዐዋቂው (ጌታ) ውሳኔ ነው።**

በቁጥር 10 ያለው ቅንፍ ማብራሪያ ነው እንጂ በቁርዓኑ ውስጥ የሌለ ነው። የሳሂ ሙስሊም ማብራሪያ ደግሞ ፍጥረት ቅዳሜ ተጀምሮ በያንዳንዱ ቀን እየተፈጠረ አዳም በ7ኛው ቀን ዐርብ ተፈጠረ ይላል፤ (ምዕራፍ 1155፤ ሐዲስ ቁጥር 6707)። ሰባት ቀን ማለት ነው።

### ለ) ሰው ከምንድርነው የተፈጠረው? ከፍትወት ጠብታ? ከሸክላና ከሚገማ ጥቁር ጭቃ? ከአፍር? ከረጋ ደም? ወይስ ከምንም?

> **3፥59 አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ፥ እንደ አዳም ብጤ ነዉ፤ ከዐፈር ፈጠረዉ፤ ከዚያም ለርሱ (ሰዉ) ሁን አለዉ፥ ሆነም።**
>
> **16፥4 ሰውን ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው፤ ከዚያም እርሱ ወዲያውኑ (ትንሣኤን በመካድ) ግልጽ ተከራካሪ ይሆናል።** [በዚህ ክፍል ስለ ሌሎችም ነገሮች መፈጠር ስለሚናገር ስለ አዳም ይመስላል።]
>
> **19፥67 ሰዉ፣ ከአሁን በፊት ምንም ነገር ያልነበረ ሲኾን፣ እኛ የፈጠርነዉ መኾኑን አያስታዉስምን?** የዩሱፍ ዓሊ የእንግሊዝኛ ትርጉም፥ We created him before out of nothing ይላል። ከእመ ዐልቦ እንደማለት ነው።
>
> **15፥26 ሰውንም ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማ ጥቁር ጭቃ በእርግጥ ፈጠርነው፡፡**
>
> **96፥2 ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)።**

አንድ ሰው[2] ይህንን አፈጣጠር ሲያብራራ ይህ የአፈጣጠር ደረጃ መሆኑን ተናግሮአል። ማለትም፥ አፈሩ አፈር፥ ጭቃው ሲለወስ፥ ሸክላው ሲደርቅ፥ የረጋው ደም ደም ከገባበት በኋላ ወዘተ፥ እያለ ሊያብራራ ሞክሯል።

ሐ) በሃይማኖት ማስገደድ አለ? ወይስ የለም? ወይስ እንደ አስፈላጊነቱ?

**2፥256 በሃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡ በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፡፡ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡**

**9፥3 (ይህ) ከአላህና ከመልክተኛዉ በታላቁ ሐጅ ቀን የወጣ አላህ ከአጋሪዎቹ ንጹሕ ነው፤ መልክተኛዉም (እንደዚሁ)፤ (ከክሕደት) ብትጸጸቱም እርሱ ለናንተ በላጭ ነዉ (ከእምነት) ብትሸሹም እናንተ አላህን የማታቅቱት መሆናችሁን ዕወቁ፤ በማለት ወደ ሰዎች የሚያደርስ ማስታወቂያ ነው፤(1) እነዚያን የካዱትንም በአሳማሚ ቅጣት አብስራቸው። [የአማርኛው ቁርኣን የግርጌ ማስታወሻው፥ ከዚህ ዓመት በኋላ ከሐዲ ከዕባን አይጎበኝም፤ ራቁቱንም አይዞርም ይላል።]**

**9፥5 የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ሰፍራ ግደሉዋቸዉ፤ ያዙዋቸዉም፤ ክበቡዋቸውም፤ ለነሱም (መጠባበቅ) በየመንገዱ ተቀመጡ፤ ቢጸጸቱም፤ ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ፤ ግዴታ ምጽዋትንም ቢሰጡ፤ መንገዳቸውን ልቀቁላቸዉ አላህ መሐሪ አዛኝ ነውና።**

**9፥29 ከነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች፤ እነዚያን በአላህ በመጨረሻዉ ቀን የማያምኑትን፤ አላህና መልክተኛዉ እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እዉነተኛዉንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነዉ ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው።**

አንዴ ማስገደድ የለም ይልና ኋላ ደግሞ ግደሉአቸው፥ አዋርዱአቸው፥ ተዋጉአቸው ይላል። ይህ ቅራኔ ካልሆነና ካልተባለ ምንድርነው? እነዚህ ጥቂት ናሙና ቅራኔና ግጭቶች ናቸው። ዶ/ር ዓሊ፥

**በእስላም ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ቁርአን ግን አንዳች ውስጣዊ አለመጣጣምም ሆነ ተቃርኖ የለበትም።**

ሲል ፍጹም እብለት መሆኑ መታወቅ አለበት። ስለ ቁርኣንን ውስጣዊና ውጪያዊ ተቃርኖዎችና ግጭቶች በርካታ መጻሕፍትና ድረ-ገጾች ይገኛሉ። ይህን ለማንበብ ለናሙና እኒህን ከግርጌ የተጠቀሱ ሁለት ድረ-ገጾች ተመልከቱ።[3]

## ምርጫውን ማን አካሄደው?

'ምርጫውን ማን አካሄደው?' በሚል ንዑስ ርዕስ ስር ከላይ ግጭት አለባቸው የሚላቸው አራቱ ወንጌላት ከብዙዎች ወንጌላት መካከል እንዴት እንደተመረጡ ሲጽፍ፥ ወንጌላት ከብዙ መካከል አራቱ በድምጽ ብልጫ እንደተመረጡና የቀሩት በሙሉ ተሰብስበው የተቃጠሉ መሆናቸውን በድፍረት ይጽፋል።

**በአንድ ወቅት ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ወንጌሎች እንደነበሩና ከነኚህ ውስጥ ቤተክርስቲያን አራቱን ማለትም የማቴዎስን፣ የማርቆስን፣ የሉቃስንና የዮሐንስን ወንጌሎች ብቻ እንደመረጠች ክርስትና ይናገራል። ቀሪዎቹ ወንጌሎች እንዲቃጠሉ ወይም እንዲጠፉና እንዲወድሙ ተደርገዋል።**

በአስገራሚ ሁኔታ ደግሞ ስለ ቁርኣን የዚህ ተቃራኒ ስለመሆኑ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፥

**እስላም ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን አንድ ነጠላ የቅዱስ ቁርአን ቅጂ ብቻ መኖሩንና ተመሳሳይ የማማረጥ ሂደት አለመደረጉን ወይም አለማስፈለጉን ይናገራል።**

ሁለቱንም አሳቦች፥ የወንጌልትን መቃጠልና የቁርኣንን አለመቃጠል እንመልከት። መጀመሪያ ወንጌላት ተሰብስበው የተቃጠሉ ከሆኑ መቃጠላቸውን በምን አወቀ? የነበረ ምስክር የጻፍውን አነበበ? ዛሬ ያሉት ሌሎች "ወንጌላት" ተብለው የሚጠሩ ጽሑፎችስ (የቶማስ ወንጌል፥ የበርናባስ ወንጌል፥ ወዘተ) ከተቃጠሉበት አመድ እንዴት ባለ ተአምር ትንሣኤ ሊያገኙ ቻሉ? ወይስ ሳይቃጠሉ የተረፉ ናቸው? እውነቱ ግን እነዚህ ሌሎቹ "ወንጌላት" ሳይቃጠሉ የተረፉ ሳይሆኑ በኋላ ተፈጥረው የተጻፉ ናቸው።

አራቱ ወንጌላት ግን ጸሐፊዎቹ ስማቸውን ባይጽፉም በሐዋርያት ወይም ከሐዋርያት ጋር በነበሩት ምስክሮች በመጀመሪያው ምዕት ዓመት የተጻፉ ናቸው። የዮሐንስ ወንጌል የዮሐንስ ስም ባይጻፍበትም የዓይን ምስክር የጻፈው መሆኑ በገጾቹ ውስጥ ይስተዋላል። ወንጌላት ሌሎች ተቃጥለው እነዚህ የተመረጡ ሳይሆኑ ከሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር በመንፈስ ቅዱስ ምሪነት የተጻፉና በቀኖና (መስፈርት፥ መለኪያ ማለት ነው ቃሉ) ተፈትሸውና አልፈው የተሰባሰቡ ናቸው እንጂ ከመቃጠል የተቤዡአቸው መጻሕፍት አይደሉም።

ደግሞ ጸሐፊው ሳያፍር የቃጠሎን ነገር መጻፉ አስገራሚ ነው። የቁርኣንን አሰባሰብ ታሪክ ከሐዲስ (የሙሐመድ ታሪኮች ስብስቦች) ስናጠና ይልቅ አንድ ቅጅ ብቻ እንዲቀር ተደርጎ የቀሩት እንዲቃጠሉ የተደረገው ወንጌላት ሳይሆኑ ቁርኣን ነው። በሳሂ አልቡካሪ መጽሐፍ ቅጽ 6 መጽሐፍ 61 አንቀጽ 4657 እና 4658 ይህ በግልጽ ተጽፎአል። የመጀመሪያው አንቀጽ የሚናገረው በጀማማ ጦርነት ጊዜ ብዙ ቁርኣንን በቃላቸው የሚያውቁ ሰዎች በመሞታቸው ሌሎቹም ሁሉ እንደነዚህ ከሞቱ ቁርኣንም አብሮ ሊጠፋ በመሆኑ ተጽፎ እንዲቀመጥ በኡመርና በአቡ በከር መካከል የተደረገውን ንግግር ነው። ከዚያ በኋላ ከተለያዩ ሰዎች፥ ከጠፍጣፋ ድንጋዮችና ከተምር ዛፍ ቅርንጫፍ ከተከተቡት ተውጣጥተው ተጻፉና መጀመሪያ አቡ በከር ዘንድ፥ እርሱ ከሞተ በኋላ ኡመር ዘንድ፥ እርሱ ከሞተ በኋላ የኡመር ልጅና ከሙሐመድ ሚስቶች አንዷ በሆነችው በሐፍሳ ዘንድ ኖረ። በ634 መሪ ወይም ከሊፍ በነበረው በኡስማን ዘመን ኢስላም በጉልበትና በጦርነት ተስፋፍቶ ተንሰራፋ። በዚሁ ጊዜ የተለያዩ ቁርዓኖች በተለያዩ ሰዎች ሲነገሩ የሰማ ሁዳይፋ የተባለ ሰው ወደ ኡስማን ቀርቦ ስጋቱን ይገልጣል። ስጋቱም አገሪቱ እየሰፋችና ሕዝቡ እየበዛ ቁርዓኑ ከተለያየ ሊፈጠር የሚችለው መከፋፈል ነው። በዚህ ጊዜ ትልቁ ስብስብ የሚገኘው ከሙሐመድ ሚስቶች አንዷ በሆነችው በሐፍሳ ዘንድ ነበርና ያ እንዲመጣ አድርጎ አራት ሰዎች መርጦ እንዲጻፍ አደረገ። ልዩነት ከኖረ ከአራቱ አንዱ የቁረይሽ ተወላጅና የሙሐመድ ቋንቋ (ዘዬ) ተናጋሪ ስለሆነ የእርሱን ቃል እንዲቀበሉም በትእዛዝ ተናገረ። ይህ ተሠርቶ በየአገሩ ከተላከ በኋላ ከዚያ በፊት በምንም ነገር ላይ ተጽፈው የነበሩት የቁርኣን ቁራጮችም ሆኑ ሙሉ ቅጅዎች ተሰብስበው እንዲቃጠሉ አዘዘ። ይህ በሐዲስ ውስጥ የትጻፍ እውነት ነው።

ዶ/ር ዓሊ ወጌሎች እንዲቃጠሉና እንዲወድሙ ተደርገዋል ሲል ይልቁን የተቃጠለው መጽሐፍ የትኛው ስለመሆኑ ይህን ታሪክ ሳያውቅ ቀርቶ አይመስለኝም። በለመደው ዘዴ ማረጋገጫ ባለማቅረብ የማያምኑት በሩቅ እንዲቆሙና ያመኑት ግራ እንዲጋቡ ለማድረግ ነው። በፈረንጆች ቆጠራ በማርች ወር 2011 የፍሎሪዳው ፓስተር ቴሪ ጆንስ ቁርኣን አቃጠለ ተብሎ በርካታዎች የሞቱበት ግርግር በአፍጋኒስታንና በሌሎችም አገሮች ሆኖ ነበር። የመጀመሪያዎቹ የቁርኣን አቃጣዮች ግን ሙስሊሞች ራሳቸው መሆናቸው በሐዲሳቸው ተጽፎአል። ፓስተር ጆንስ ቁርኣንን ማቃጠሉ በኔ እይታ ጅልነት ነው። የሰውየው አሳብ የመጽሐፉን መልእክትና የመጽሐፉ ተከታዮች የሆኑቱ ጽንፈኞች የሚወስዱትን ጸረ አሜሪካ አቋም ለማጋለጥ ቢሆንም አንድ ጊዜ እንኳ ከዳር እስከ ዳር አንብቦ

---

[2] መሐመድ ሰዲቅ (የዲቪዲ ስርጭት በአማርኛ)።

[3] http://www.answering-islam.org/Quran/Contra/ http://wikiislam.net/wiki/Contradictions_in_the_Qur'an.

ያልተወጣውን መጽሐፍ ከሚያቃጥል አንብቦ ስሕተቶቹን ቢያሳይ የተሻለ ውጤት ይኖረው ነበር። እርሱም ሆነ ሌሎች ክርስቲያኖች ማድረግ ያለባቸው ማንበብና መመርመር ነው።

## ኦሪጂናል ቋንቋ

ዶ/ር ዓሊ በመቀጠል 'ኦሪጂናል ቋንቋ?' በሚል ንዑስ ርዕስ ስር፥

> **የማቴዎስ ወንጌል መጀመሪያ የተጻፈበት ኦሪጂናል ቋንቋ የዕብራይስጥ ቋንቋ መሆኑን ክርስትና ይናገራል። ግና የዕብራይስጥ ኦሪጂናል ቅጂው የትም የለም፤ ፈጽሞ ጠፍቷል። ዛሬ የሚገኘው ከዚህ ከጠፋው ቅጂ በሌላ ቋንቋ የተተ ረጎመ የትርጉም ቅጂ ብቻ ነው።**

ይላል። ይናገራል የሚለው ክርስትናን ነው። ይህ ምሑራዊ አጠቃቀስ አይደለም። ሰው ተናገረ ካለ "ማን?" እንዳይባል ይሆናል እንዲህ ያለ "ክርስትና ይናገራል" የሚል ቋንቋ መጠቀሙ። የማቴዎስ ወንጌልም ሆነ ሌላ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በመጀመሪያ በዕብራይስጥ አልተጻፉም። ቀደም ሲል ስለ አራማይስጥ በተነገረው ክፍል እንዳልኩት የዘመኑ የደረጀ የጽሑፍ ቋንቋ ግሪክ በመሆኑ ማቴዎስንም ጨምሮ አዲስ ኪዳን በመላው በግሪክ ቋንቋ ነው የተጻፈው እንጂ በዕብራይስጥ አልተጻፈም። ክርስትና የተባለው ተናጋሪ ይህንን አላለም። የመናገሪያ ቋንቋቸው አራማይስጥ ስለሆነ ኦሪጂናሉ ጽሑፍ ዕብራይስጥ ነው ብሎ መገመትና መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ማቅረብ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ይህ ጸሐፊ አስረጅ ስለማያቀርብባቸው ጉዳዮች በግድ የለሽነት አባባሎችን መወርወሩ መጽሐፍ ቅዱስን ለማቆሸሽና ለማስነወር ነው። የሚያሳዝነው ይህንን እርሱ የሚያንቋሽሸውን መጽሐፍ የራሱ ነቢይ አንቋሽሾት ነበር ወይ? ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ አይደለም ነው። ይህንን በቀጣዩ ክፍል እንመለከታለን።

ከዚሁ ጋር በማነጻጸር (መጽሐፉ ራሱ የንጽጽር አይደል?) ስለ ቁርኣን ሲናገር እንዲህ ይላል፥

> **ከትክክለኛነት መመዘኛ አኳያ የትኛው መጽሐፍ ነው ይበልጥ አስተማማኙ? ኦርጂናሉ የጠፋ መጽሐፍ ወይስ ኦሪጂናሉ ዛሬም የሚገኝ መጽሐፍ? ለትክክለኛነቱና ለተኣማኒነቱ የትኛውን የበለጠ ይመርጣሉ?**

አሉ የሚባሉት ጥንታዊ የቁርኣን ቅጂዎች ከሙሐመድ ሞት በኋላ ከ100 እስከ 200 ያህል ዓመታት በኋላ የተጻፉ ናቸው። በታሽኬንት የሚገኘው የስማርካንድ ጽሑፍ ጥንታዊ የሚባለው ሆኖ በ800 ዓ. ም. ገደማ የተጻፈ ነው። ዶ/ር ዓሊ "ኦሪጂናሉ ዛሬም የሚገኝ" ሲል ሸንገላ ነው። ኦሪጂናል የሚለው ይህንን ከሆነ ይህ ኦሪጂናል አይደለም። ኡስማን ያስጻፈውም እንኳ የለም እንጂ ኦሪጂናል ሊሰኝ አይችልም። ኦሪጂናል መሰኘት የነበረባቸው የሉም እንጂ እንዲቃጠሉ የተደረጉት በድንጋይም፥ በልጣጭም፥ በብራናም የተጻፉት የመጀመሪያዎቹ ነበሩ። እነዚያ ቢኖሩና ቢተያዩ ታሪኩ ሌላ ሊሆን ይችል ነበር። ጸሐፊው ኦሪጂናል የሚለው ይህንን ጥንታዊ የሚባለውን ወይም በራሱ ቋንቋ "ኦሪጂናሉ ዛሬም የሚገኝ መጽሐፍ" የሚለው የስማርካንድ ጽሑፍ መሆን አለበት።

## ቅጂዎች?

በመቀጠል 'ብዙ የተለያዩ ቅጂዎች ወይስ አንድ ብቸኛ ቅጂ?' በሚል ንዑስ ርዕስ ስር ጸሐፊው እንዲህ በማለት ይጀምራል፥

> **የክርስትና መጽሐፍ ቅዱስ አያሌ የተለያዩ ቅጂዎች ያሉት ከመሆኑም ባሻገር በማያቋርጥ የመለዋወጥ ሂደት ውስጥ ያለና ከጊዜ ወደ ጊዜ ክለሳና ማሻሻያ የሚካሄድበት መጽሐፍ ነው።**

በተለይ ክለሳ፥ ማሻሻያ፥ እና የማያቋርጥ የመለዋወጥ ሂደት የሚሉት ቃላት የሐሰት ክስ ናቸው። በምሑራዊ አቀራረብ ማስተያየት ማዳላት መሆን የለበትም። መጽሐፍ ቅዱስን፥ ለምሳሌ፥ አዲስ ኪዳንን ማስተያየት የሚፈልግ ሰው የአሁኑን የዐረብኛ ቁርኣን በ800 ዓ. ም. ከተጻፈው ጋር እንደሚያስተያይ ሁሉ በዐረብኛ ወይም በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ የተጻፈውን ትርጉም ሳይሆን ዛሬ ያለውን የግሪክ አዲስ ኪዳን ከቀዳሚ ቁርጥራጭ ጽሑፎች ሰነዶች ጋር ነው ማስተያየት ያለበት። ጸሐፊው ይህን አድርጎ ስሕተቶች አገኘሁ ካለ አላቀረበም። ከአጻጻፉ እንደሚታየው የማድረጉ ብቃትም የለውም። በማያቋርጥ የመለዋወጥ ሂደት እያለፉ የሚላቸው የተለያዩ ቅጅዎች ቅጅዎች ሳይሆኑ ትርጉሞች ናቸው። እነርሱም በማያቋርጥ የመለዋወጥ ሂደት እያለፉ ሳይሆኑ የተተረጎሙበት ቋንቋ ነው ሳያቋርጥ የሚለዋወጠው። በቁርኣንም ስላሉት ልዩነቶች በዝርዝር ከታች ባለው ድረ ገጽ[4] ተመልከቱ። ወደ እንግሊዝኛ በተለያዩ ጊዜያት የተተረጎሙ የቁርኣን ትርጉሞችም ቁጥር ከ20 ሳይበልጥ አይቀርም። እኔ 16 ቆጥሬአለሁ። እና የሁሉም ቃል አንድ ነው? አይደለም። ይህ የትርጉም ጉዳይ ነው።

ጸሐፊው የተለያዩ ቅጂዎች የሚለው የተለያዩ ትርጉሞችን ከሆነ ቅጅ ማለት የለበትም። በአማርኛ ብቻ እንኳ አሁን ወደ አምስት ያህል ትርጉሞች አሉ። በእንግሊዝኛ በመቶዎች ይቆጠራሉ። ይህ የሆነው ቋንቋ በዘመናት ውስጥ እንደ ሐውልት ቆሞ የሚቀር ሳይሆን የመለወጥ፥ የማደግ፥ የመስፋት፥ የመሸብሸብና የመጥፋት ባህርይ ስላለው ነው። ቁርኣንም ወደ ሌላ ቋንቋ ሲተረጎም ይህ እንደሚሆን የታወቀ ነው። ያለዚያ አሁን በየቋንቋው ትርጉሞች እንደሚደረገው በቅንፍና በግርጌ ማስታወሻ ማብራሪያ መጻፍና፥ 'ይህን ሲል ይህን ማለቱ ነው' ብሎ ማብራራት የተለመደ ይሆናል። በአማርኛው ቁርኣንም ቅንፎችና የግርጌ ማስታወሻዎች ቁጥር እጅግ ብዙ ነው። ይህ የሆነው ራሱ ዐረብኛውም ከሺህ አራት መቶ ዓመት በተጻፈበት ቋንቋ ደርቆ አለመቅረቱን የሚመሰክር ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ክለሳና ማሻሻያ የሚደረግበትና በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ውስጥ ያለ መጽሐፍ ሳይሆን ቋንቋ ነው በለውጥ ሂደት ውስጥ እያለፈ የሚኖረው። መልእክቱ እንዲተላለፍ ከተፈለገ ቋንቋ ሲለወጥ ቃላት ሊስተካከሉና ሊለወጡ የግድ ነው። ያለዚያ በቅንፍ ውስጥ `እንዲህ ማለት ነው` እያሉ ሲጽፉ መኖር ነው። ጸሐፊው ምሳሌ ቢሰጥና፥ `የቆየው የግሪኩ ጽሑፍ 12 ሐዋርያት የሚለውን የዘንድሮው ደግሞ 36 ሐዋርያት በማለት ከልሶታል፤ አሻሽሎታል` የሚል ወይም ይህን የሚመስል ክስ ወይም ማስረጃ ቢያቀርብ እውነትም መጽሐፍ ቅዱስ ክለሳ ይደረግበታል ሊባል ይችላል። ግን በዘመናት ውስጥ ቀድሞ ከተጻፈው በቋንቋ መግለጫ እንጂ በይዘት የተለየ ነገር ማቅረብ ስለማይችለው ነገር ሲጽፍ ጸሐፊው የራሱን ስንፍና ማጋለጡ ነው።

## ሐዋርያ ወይስ ነቢይ?

ጸሐፊው ሐዋርያ ወይስ ነቢይ በሚል ንዑስ ርዕስ ስር ኢየሱስ ነቢይ አለመሆኑን ክርስትና ስለማስተማሩ ይህን ይላል፤

> **ዮሐንስ፣ ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ወንጌሎቻቸውን ለመጻፍ ከእግዚአብሔር ራእይ የተገለጸላቸው ሲሆን፣ የክርስትና እምብርት የሆኑት ኢየሱስ ራሳቸው ግን ከእግዚአብሔር ምንም ራእይ እንዳልተገለጸላቸው ክርስትና ይናገራል።**

ይህ 'ክርስትና ይናገራል' እያለ ጸሐፊው ለሚለጥፈው ነገር ይኸው ማስረጃው እያለ ቢያቀርብ ጥሩ ነበር። ለነገሩ ንዑስ ርእሱ ራሱ ግራ የገባው ነው። ኢየሱስ ነቢይ መሆኑን ጸሐፊውና ሃይማኖቱ ይቀበላል። ግልጽ ባይሆንም እንደተረዳሁት ግን ነቢዩ (ኢየሱስ) ቃል ሳይቀበል ሐዋርያቱ ስለ እርሱ ጻፉለት ማለቱ ይመስላል። እዚህም ላይ ሁለት ስሕተቶችን እናጢን።

---

[4] *http://www.answering-islam.org/Green/seven.htm/*



© ዕዝራ ስነ ጽሑፍ 2013 ቃልህ ተገኝቶአል እኔም በልቼዋለሁ፤ አቤቱ የሠራዊት አምላክ ሆይ፥ በስምህ ተጠርቻለሁና ቃልህ ሐሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ። ኤር. ፲፭፥፲፮ ባለቤትነቱን ሳይወስዱ ማባዛትና ማደል ይፈቀዳል።

አንደኛ፥ ‘ክርስትና ምንም ራእይ እንዳልተገለጸላቸው ይናገራል’ ያለው ጸሐፊው ውሸቱን ነው። ክርስትና ወይም አዲስ ኪዳን እንዲያውም የሚናገረው ኢየሱስ እንደ ብሉይ ወይም አዲስ ኪዳን ነቢያት ነቢይ ሳይሆን እርሱ ሰው የሆነ፥ ሥጋን የለበሰ አምላክ መሆኑን ነው። ደግሞም ነቢይም ሐዋርያም መሰኘቱም በእርግጥ ተጽፎአል። እነዚህ ግን በማንነቱ ላይ የተጨመሩ ሥራውን የገለጡ ቃላት ናቸው እንጂ እርሱ ከቀድሞ የነበረ ሥጋ የለበሰ ቃል ነው። ለነገሩ ኢየሱስ ቃል የተሰኘው በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አይደለም። ጸሐፊው ልብ ያላለው ወይም አውቆ የደበቀው እውነት በቁርኣንም ኢየሱስ የአላህ ቃል እና የአላህ መንፈስ መሰኘቱን ነው። በ4፥171 ያለው ቃል ይህንን ያረጋግጣል።

> **እላንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ፤ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ፣ የአላህ መልክተኛ፣ ወደ መርየም የጣላት (የሁን) ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው፤ በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉም፤ ተከልከሉ ለናንተ የተሻለ ይሆናልና፤ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው። መመኪያም በአላህ በቃ።**

ጥቅሱ አማልክት ሦስት ናቸው አትበሉ፤ አላህ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው በማለት ክርስቲያኖችን ሦስት አማልክት አምላኪ አድርጎ ያቀርባል። ሙሐመድ ሥላሴን የተረዳው እንደዚያ ስለሆነ ነው። ቀደም ሲል እንዳየነውም ሦስቱ ያላቸው እግዚአብሔር፥ ኢየሱስ እና ማርያም ናቸው። ልጅ ያለው ሲባልም የሥጋ ልጅን፥ ማለትም እግዚአብሔርና ማርያም በሥጋ ተገናኝተው እንደተወለደ ልጅ ማለቱ ነው። ሌላው ይህ አንቀጽ የሚለው ኢየሱስ ቃል መሆኑን ነው፤ ወደ ማርያም የጣላት ቃል። ቃሉ፥ ‘ቃሊማቱላህ’ ኢየሱስ የአላህ ቃል መሆኑን መግለጡ ነው። በዚህ ጥቅስ ቃሉ ብቻ ሳይሆን የአላህ መንፈስም (ሩሁላህ) ተሰኝቶአል፤ የይህ ቃል በሌሎችም የቁርኣን ክፍሎች ተጠቅሶአል፤ 2፥87 እና 253፤ 16፥102።

ኢየሱስ ቀድሞ የነበረው ቃል ከሆነ ጸሐፊው እንዳለው ኢየሱስ “ከእግዚአብሔር ምንም ራእይ እንዳልተገለጸላቸው” ክርስትና አይናገርም። እግዚአብሔርን ማንም ያየው የለም፤ አንድ ልጁ ግን እርሱ ግን ተረከው፤ ይላል፤ ዮሐ. 1፥18። ሥጋ ከለበሰው የቀደመ ቃል በላይ ማን ይተርከው? ራሱ ቃል ቢሆንም ቃልን መቀበሉን ደግሞ ራሱም ተናግሮአል። በዮሐ. 17፥8 ደግሞ ጌታ፥ *የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፥ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ* አለ። የተቀበለውና የሰጠው ቃል አለ ማለት ነው። ይህንን ነው ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠውና እነርሱም የተቀበሉት። ይህንን ነው እነርሱም የጻፉትና ያስተላለፉት። ነቢዩ ምንም አለመቀበሉ የሚለው አባባል ቅጥፈት ነው።

ሁለተኛው ስሕተት፥ እርሱ አስተማረ እንጂ አልጻፈም፤ ደቀ መዛሙርቱና ከዓይን ምስክሮች የሰሙቱ ያስተማረውንና ያደረጋቸውን ነገሮች ጻፉ የሚለው ነው። ጸሐፊው ዶክተር ዓሊ ሚዛኑን የሳተበትን ነገር ተመልከቱ፤ ሙሐመድም እኮ ጅብሪል ተናገረኝ ያለውን ሌሎቹ ሰሙና ሸምድደው ቆይተው ኋላ ያ የሸመደዱት ቃል በቅጠልም፥ በዛፍ ልጥም፥ በድንጋይም፥ በአጥንትም፥ በብራናም ተጻፈ እንጂ እርሱ ራሱ አልጻፈውም። እርሱ ራሱ እንዳልጻፈው እያወቀ ስለ ሙሐመድ ሌሎች ከእርሱ የሰሙትን መጻፋቸውን በአድናቆትና በአንክሮ እየተቀበለ ስለ ኢየሱስ ከእርሱ የሰሙትና ያዩት የጻፉትን አለመቀበሉ ነው የሚያስደንቀው ስሕተት። ይህ ይደንቃል። ሙሐመድ አለመጻፉ ከኢየሱስ አለመጻፍ ልዩነቱ ምንድርነው?

(. . . . ይቀጥላል)



*ዘላለም መንግሥቱ © 2013 (፪ሺ፱፮) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት*

## *ደንግጬ ነበር*

*አንድ ሽማግሌ ዶክተሩን ለማየት ሄዶ ምርመራ ከተደረገላቸው በኋላ ውጤቱ መጣና ሊነግራቸው ጀመረ። “ጥሩም መጥፎም ነገር አለኝ፤ የትኛውን ላስቀድም?” አለ።*

*“መጀመሪያ መጥፎውን አውጋኝ እስኪ” አሉት።*

*“መጥፎው ዜና የምርመራው ውጤት የሚያስረዳው ካንሰር እንዳለብዎት ነው። ከዚህ በኋላ ሊኖሩ የሚችሉት ሁለት ዓመት ብቻ ነው” አላቸው።*

*“በሁለት ዓመት አበቃልኝ ማለት ነዋ! ከዚህ መርዶ በኋላ ምን መልካም ዜና ልትነግረኝ ታስባለህ?” አሉት።*

*“ጥሩው ነገር ደግሞ ከካንሰሩ ሌላ አልዛይመርስ ጀምሮዎታል፤ እና ከቀን በኋላ ካንሰር እንዳለብዎትና አሁን የነገርኩዎትን በሙሉ ይረሱታል” አላቸው።*

*“አልዛይመርስ? አይ፥ አልዛይመርስ ከሆነስ ደህና ነው፤ እኔኮ ደንግጬ ነበር ካንሰር አለብህ ያልከኝ መስሎኝ” አሉት። እዚያው ረሱለት።*

* * * * *

## *ሁለቱ እብዶች*

*ሁለት እብዶች ከአማኑኤል ሆስፒታል ዘበኛውን አታልለው ለማምለጥ ይመካከራሉ። የሚወጡበትን ቀን፥ ሰዓት፥ የአወጣጣቸውን ሁኔታ፥ ለዘበኛው ምን እንደሚሉ፥ ሌሎች ሰዎች ቢኖሩ ምን እንደሚያደርጉ መከሩ። የሚለብሱትን ልብስ ሁሉ ካሰናዱ በኋላ በተነጋገሩበት ቀን በምክራቸው መሰረት ዝግጅታቸውን ጨርሰው፥ እንደ ዶክተሮች ለብሰው፥ የልብ ምት ማዳመጫ እስቴቶስኮፕ ሳይቀር ማጅራታቸው ላይ ጣል አድርገው ወደ ዋናው የግቢው በር መሄድ ጀመሩ። ወደ በሩ ሲደርሱ ዘበኛው ሁሌም በሚቆምበት ቦታው የለም። “አይይ! ዘበኛው ከሌለማ ማንን እናታልላለን?” አለ አንዱ። ሁለተኛውም፥ “አይይ ዕቅዳችን ተበላሸ” ብሎ በመጥፋት ፋንታ ወደነበሩበት ክፍል ተመለሱ።*